ቴምድሮስ

ታሪካዊ ድራማ

ተጻፈ

ከደጃዝማች

ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት።።

አዲስ አበባ።።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ማውጫ፤

መግቢያ።። 1
የታሪኩ መግቢያ።። 1
የቴያትሩ ክፍሎች አጭር ማስረጃዎች።። 2
ማስገንዘቢያ።። 3
የተጫዋቾች ዝርዝር 3
ቴዎድሮስ።። 5
ክፍል አንደኛ።። 5
፩ኛ ትርኢት።። 5
፪ኛ ትርኢት።። 8
ክፍል ሁለተኛ።። 10
፩ኛ ትርኢት።። 10
፪ኛ ትርኢት 18
ደጃዝማች ካሣ ወታደሮቻቸውን ይጐበኛሉ።። 18
፫ኛ ትርኢት።። 22
ካሣና ተዋበች (ካሣ ከውጭ ይገባል)።። 22
ክፍል ሦስተኛ 29
፩ኛ ትርኢት 29
፪ኛ ትርኢት።። 30
፫ኛ ትርኢት።። 32
፭ኛ ትርኢት።። 40
፮ኛ ትርኢት።። 42
፯ኛ ትርኢት።። 43
ክፍል አራተኛ።። 46
፩ኛ ትርኢት።። 46
አምስተኛ ክፍል።። 55
፩ኛ ትርኢት።። 55
፪ኛ ትርኢት።። 57
፫ ትርኢት።። 59

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ክፍል አምስተኛ፡፡ 60
፬ኛ ትርኢት፡፡ 61
፭ኛ ትርኢት፡፡ 66
፮ኛ ትርኢት፡፡ 73
፯ኛ ትርኢት፡፡ 83
አፄ ቴዎድሮስ፡፡ 83
፬ኛ ትርኢት፡፡ 85
ጄኔራል ናፒዬር (በትካዜ አነጋገር)፡፡ 85
፭ኛ ትርኢት፡፡ 87
ጄኔራል ናፒዬር፡፡ 87

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

መግቢያ::

ስለ ምግባር መደርጀትና መታረም በተለየ የቴያትር ድርስት ጥቅም መስጠቱን በማወቅ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባገራችን ይህ ሥራ እንዲለመድና እንዲስፋፋ ከብዙ ጊዜ ዠምረው ለደራሲዎች የሚያደርጉትን ድጋፍ መዠመሪያ ማስታወስ ይገባል።

ይህ የዐፄ ቴዎድሮስን ታሪክ የሚያሳይ ቴያትር ስለ አገር ፍቅርና ስለ ወገን ክብር ስለ አንድነት ጥቅም ለኢትዮጵያዊ ሁሉ ንጹሕ የሆነውን ስሜት እንዲያስገኝ ዋና ምኞቴ ነው።

ዐፄ ቴዎድሮስ ሀሳባቸው ከዘመናቸው የቀደመ በመሆኑ ብዙ ተቀባይና ረዳት ባለማግኘት ከፍ ያሉ እንቅፋቶች ተፈጥረውባቸው በብርታትና በጎያል ሲታገሉ ዘመነ ንግሣቸው በምሬት ተፈጸመ።

እንዲህ እንደርሳቸው ላገር ጥቅምና ለሕዝብ ኑሮ የሚበጁ አዲሶች አሳቦች የወጠኑና የማሻሻል ሥራ የሞከሩ መሪዎች ሁሉ ብዙ እንቅፋቶች ገጥመዋቸው ብርቱ ትግል እንዳስፈለጋቸው ሰፊ በሆነው በዓለም ታሪክ ውስጥ ብዙ አስረጂዎች ይገኛሉ። ነገር ግን አሳባቸውን በመልካም አኳኋን ለመፈጸም የቻሉት መሪዎች ጎይልን ከዘዴ ጋራ ብርታትን ከትዕግሥት ጋር አድርገው እምነትንና ተስፋን ፍቅርንም ጨምረው የሠሩት እንደ ሆኑ የታወቀ ነው።

በብዙ ድካምና በብዙ መከራ የተገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት እንዲሁም በስንት ተጋድሎና ፈተና ጸንቶ ያለው የኢትዮጵያ ነፃትና ክብር ሁል ጊዜም በንጉሠ ነገሥቶቿ ከፍተኛ ምግባርና ባርበኞቿ ልባዊነት፥ በሕዝቡም ብርታትና ታማኝነት ተጠብቆ፥ እንደሚኖር አሁን በቅርቡ ያለፈው ያጅቱ ዓመታት ፈተና በቀድሞ ታሪክ ከሚገኙት አያሌ ማስረጃዎች ጋራ ተጨምሮ ለዘለዓለም ምስክር ሆኖ ይኖራል።

በወገኖቹ ሙያና ባባቶቹ ምግባር በሚገባ ለመመካት የሚችል ታሪክ ያለው እንደ ኢትዮጵያዊ ያለ ሕዝብ የኋላውን እያስተዋለ ወደ ፊት በማሰብ በደጉም ሆነ በክፉም ዕድሉ ቢሆን እርምጃውን በተስፋና በእምነት ይቀጥላል። ቁም ነገርንና ትውልድን አብልጦ በማሰብ መሠረት ይዞ ስለሚጓዝ መጭን ጊዜ በተስፋና በእምነት ለማስተዋል ከመቻሉ በላይ ከተመልካቾቹም ፍቅርና ከበሬታን እንደ ሚያገኝ አይጠረጠርም።

ግ ተ ሐ።

የታሪኩ መግቢያ::

ከብዙ ሺሕ ዓመት ዠምሮ ነፃነቱንና ክብሩን ጠብቆ ባፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ መንግሥታት መካከል በጣም ከፍ ያለ ስም የነበረው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ባ፲፰ኛው መቶ ዘመን ውስጥ አንድነቱን አጥቶ ነበር። በጐንደር ቤተ መንግሥት ንጉሠ ነገሥቱ ለስመ ዘውዱን ጭኖ ተቀምጦ ሥልጣኑ ግን በመሳፍንቶች እጅ ገብቶ እንደ አካልና ጎያል የነበረው የቀድሞ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግዛት የመከፋፈልና የመለያየት የመድከምም መልክ ይዞ በመታየቱ ያገሪቱ ነፃነት በታላቅ አደጋ ላይ ደርሶ ነበር።

በዚያን ጊዜም ከዙሪያው የሚጠባበቁት ያገራችን ጠላቶች ይልቁንም በሰሜንና በምሥራቅ በኩል የወረራ ሥራ በመሞከራቸው በብዙ ቦታ ወሰን እያለፉ አገር መያዝ ዠምረው ነበር።

መሳፍንቶቹም ምንም እንኳን አገሩን በሙሉ ፀጥ አድርገው ለመግዛት ባይችሉ የውጭን ጠላት ለመከልከል በተቻላቸው አልቦዘኑም ነበር። ስለሆነም በዚህ ባደገኛ እመን የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድ

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

አድርጎ የሚመራውና ጠላትንም የሚያሳፍር ብርቱ ሰው እንደሚያስፈልገው ይታወቅ ነበርና እነሆ ካሳ የተባለ የቋራ ተወላጅ ሰው በውልደት ቀጥታ በተለየ ላልጋው ወራሽነት የታጨ ሳይሆን በተሙላ ስጦታውና በጀብዱው ስሙን አስነሥቶ ድል በድል እየተራመደ ዘውዱን ጨብጦ በዳግማዊ ቴዎድሮስ ስም ነገሠ። ላልቶ የነበረውን አንድነት እንደ ገና አድሶ እስከ ዛሬ ፀንቶ ያለውን ያንድ ንጉሠ ነገሥት ግዛት አቋቋመ።

የቴያትሩ ክፍሎች አጭር ማስረጃዎች።

ደጃዝማች ካሳ ሸፍተንትን ትተው የእቴጌ መነንን የልጅ ልጅ የራስ ዐሊን ልጅ ወይዘሮ ተዋበችን አግብተው በሰላማዊነት በቤተ መንግሥት ገብተው ጥቂት ጊዜ እንደ ቆዩ ድኅነታቸውን ምክንያት በማድረግ የቀድሞውን ጠብና ቂም ባለመርሣት መሳፍንትና መኳንንት በየጊዜው ክብራቸውን በማኰስስ ሳልስቆጫቸው ምሬት ገብቷቸው ሚስታቸውን ወይዘሮ ተዋበችን ይዘው እንደ ገና ሸፈቱ ይባላል።

፩ኛ ክፍል። በጐንደር ቤተ መንግሥት።

የደጃዝማች ካሳ መሸፈት እንደ ተሰማ የንጉሠ ነገሥት ስም የነበረውን ዮሐንስ ፫ኛ አግብተው እቴጌ የነበሩት እቴጌ መነን (የራስ ዐሊ እናት) ራስ ዐሊን ጨምረው ከመኳንንቶቻቸው ጋራ ይማከራሉ ካሳን እንዲይዝ ከደጃዝማች ወንድይራድ ይታዘዛል። እርሱም በመመካት ይቀበላል።

፪ኛ ክፍል። በደጃዝማች ካሳ ሰፈር።

(ሀ) ደጃች ካሳ ሸፍተው በሠፈራቸው ከባለቤታቸው ከወይዘሮ ተዋበችና ከታማኝ አሽከሮቻቸው ከገብርዬ ከገልሞ፣ ከዓለሜ ጋራ ሆነው ይመካከራሉ።

(ለ) የደጃች ወንድይራድን መምጣት እንደ ሰሙ አርበኞቻቸውን በጋለ ቋንቋ ካበረታቱ በኋላ ለመግጠም ቁርጠው ይነሣሉ።

(ሐ) ከሚስታቸው ሲሰነባበቱ ሴቷ በዚህ ባባትና በባል አጋጣሚ ጠብ ኀዘናቸውን እየገለጡ ሁለቱም ይወያያሉ።

(መ) ወንድይራድ ይማረካል።

(ሠ) በጐንደር ቤተ መንግሥት ወሬው እንደ ተሰማ እቴጌይቱ ይዘምታሉ እርሳቸውም ይማረካሉ።

(ረ) ደጃች ካሳ ድል በድል እየገሠገሡ በደምቢያ በጐርጐራ በደረስጌ እቴጌ መነንን ራስ ዐሊን ደጃች ውቤን ሁሉንም በተራ ድል መትተው ዳግማዊ ቴዎድሮስ ተብለው የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ይጭናሉ።

(ቀ) የንጉሠ ነገሥቱ ዐዋጅ ይነገራል።

፫ኛ ክፍል። በሸዋ ቤት መንግሥት።

(ሀ) ንጉሥ ኃይለ መለኮት ታመዋል ያሜ ቴዎድሮስን መምጣት እንደ ሰሙ ከሸዋ ባላባቶችና ከመኳንንቶቻቸው ጋር ይመካከራሉ። ለመመከት ቊርጥ አሳብ ያደርጋሉ።

(ለ) ዐሜ ቴዎድሮስ ዐሜ ምኒልክን ማርከው ይዘዋቸው ይሄዳሉ።

፬ኛ ክፍል። ዘመነ ንግሥ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

(ሀ) ዐፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን በመላ አስገብረው የጥንቱን አንድ የን ነ መንግሥት ካቋቋሙ በኋላ ስላስተዳደር ያቀቱን አሳባቸውን ይደርድራሉ።

(ለ) ይህን አሳባቸውን ለመፈጸም ሥራ እንደ ገ/መሩ አውራጆቹ ሁሉ የመሸፈታቸው ወሬ እየተከታተለ ይመጣላቸዋል በዚህም ጊዜ ብስጭት ገብቷቸው የጭካኔ መንፈስ ያድርባቸዋል።

(ሐ) የጋረድና የቤል ሞት ይታያል

(መ) አንድ ባሕታዊ መጥቶ ስለ ሕዝቡ ሥቃይና ስለ ጭካኔያቸው በድፍረት አነጋገር ይወቅሳቸዋል እርሳችወ ግን ምክሩን ሳይቀበሉ የባሰውን ይጨክናሉ።

(ሠ) ከእንግሊዝ ቆንሲል ከካፒቴን ካሜሮን ጋራ ይጣላሉ ፈርንጆቹንም ሁሉ ያስሯቸዋል።

፫ኛ ና ፮ኛ ክፍል። መቅደላ ከእንግሊዞች ጋራ ጦርነት።

(ሀ) በመቅደላ ዐፄ ቴዎድሮስ ከታማኝ አሽከሮቻቸው ጋራ ስለ ጦርነቱ ዐቅድ እየተመካከሩ ምሬታቸውንም ይገልጻሉ።

(ለ) ፊታውራሪ ገብርዬ ከሞቱ በኋላ ሚስታቸው እቴጌ ጥሩ ወርቅ እርቅ እንዲጠይቁ ይመክሯቸዋል።

(ሐ) ዐፄ ቴዎድሮስ አልማረክም ብለው ሕይወታቸውን በገዛ እጃቸው ያጠፋሉ።

(መ) እንግሊዞችም ለሬሳው ሰላምታ ይሰጣሉ። እቴጌ ጥሩ ወርርቅ ያለቅሳሉ። ጄኔራል ናፒዬ አጭር ንግግር ያደርግና ቴያትሩ በዚሁ ይፈጸማል።

ማስገንዘቢያ።

ይህ የቴያትር ጽሑፍ ምንም እንኳን መሠረቱ ታሪክ ቢሆን ለቴያትር እንዲስማማ ዋናዎቹን ምዕራፎች ይመለከታል እንጂ ታሪኩን በሙሉ የሚናገር በትክክል የሚከተል አይደለም። የቴያትር ድርስትና የታሪክ ድርሰት ሁለት ልዩ ነገሮች ከመሆናቸው በላይ ታሪክ በተለየ የሚያስገድደውን ጥልቅ ምርመራና እርግጠኛነት ቴያትር እንደማይጠይቅ አንባቢ አይስተውም።

አጻጻፉንም በግጥም ስልት ያደረግሁት ለቴያትሩ መልክ ለመስጠት ስሜትና ቅልጥፍና ያለው አነጋገር በመፈለግ ብቻ ስለ ሆነ የግጥሙ አካሄድና ዜማው ባንዳንድ ቦታ ላይ ያልተካከለ ሆኖ ይገኝ ይሆናል።

ይህ የቴያትር ድርሰቱ ስላገራቸው ነጻነትና ክብር ሲታገሉ ሕይወታቸውን ለሠዉላት ጀግኖችና በሰላም ጊዜም ሆነ በፈተናም ሰዓት ቢሆን ለኢትዮጵያ መብትና ልማት በመታገል ብዙ ድካም ላደረጉላት ሁሉ መታሰቢያ ይሁልኝ።

ደራሲው።

የተጫዋቾች ዝርዝር

፩ እቴጌ ጣይቱ (የራስ ዐሊ እናት)

፪ ራስ ዐሊ

፫ መኳንንት

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

፬ መነኰሴ

፭ ደጃዝማች ወንድይራድ

፮ ደጃዝማች ካሳ (በኋላም ዐፄ ቴዎድሮስ)

፯ ፊታውራሪ ገብርዬ

፰ ባላምባራስ ገልሞ

፱ ደጃዝማች ዓለሜ

፲ ወይዘሮ ተዋበች (በኋላ እቴጌ)

፲፩ ጥሩ ወርቅ (እቴጌ)

፲፪ ባሕታዊ

፲፫ ንጉሥ ኃይለ መለኮት

፲፬ አቤቶ ምኒልክ

፲፭ አቶ ዳርጌ

፲፮ አቶ ሰይፉ

፲፯ አቶ ሀብቴ

፲፰ አቶ አንዳርጋቸው

፲፱ አቶ ሀብተ ማርያም (የጠራው)

፳ አቶ ግርማሜ

፳፩ አቶ በዛብህ

፳፪ አቶ ናደው

፳፫ አቶ አዝብጤ

፳፬ አቶ ሽዬ ዘረፉ

፳፭ ጆነራል ናፒዬር

፳፮ ካፒቴን ካሜሮን

፳፯ የልፍኝ አሽክሮች

፳፰ ገረድ

፳፱ ወታደሮች

፴ መልእክተኞች

፴፩ እስረኞች

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

፴፪ አቡነ ሰላማ

፴፫ የእንግሊዝ ወታደሮች

፴፬ ልጅ ጋረድ

፴፭ ሚስተር ቤል

፴፮ አንድ ባላገር

፴፯ ደጃች ውቤ (የሰሜን ገሸር ና ባሕር ነጋሽ)

፴፰ ልጅ ዓለማየሁ ቴዎድሮስ ልብሱና መሣሪያው የዚያው ዘመን ነው።

ቴዎድሮስ።

ክፍል አንደኛ።

፩ኛ ትርኢት።

በጎንደር ቤተ መንግሥት በእቴጌ መነን እልፍኝ እቴጌ መነን ራስ ዐሊ አንድ መነሡሴ መኳንንቶች አንድ የልፍኝ አሽከር።

እቴጌ መነን (የራስ ዐሊ እናት)።

ኧረ ለመሆኑ ምን ይሆን አሳቡ

ሸፍቶ የሄደው ከነቤተ ሰቡ።

ራስ ዐሊ።

ሰውዬው ኩሩ ነው የተነፋ ልቡ

ይዞ ማዋረድ ነው ይበርዳል ጥጋቡ።

ከመኳንንቱ አንዱ።

አንዴ ከተያዘ ከገባ በጃችን

አንጨክንም ከቶ በገዛ አማቻችን።

እርሱም በበኩሉ በኛ ያዝን ይሆናል

እርቅ ሰላም አርጎ እምተው ይገባናል።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

መንሱሴው።።

ሰውዬው ብርቱ ነው ስሙ የተጠራ

ጉበዝ እኔ ነኝ ባይ ኃይልን የማይፈራ።።

በዘዴ በትዕግሥት ማባበል ይሻላል።።

በጎይል ብንለው በጣም ያውከናል።።

እቴጌ መነን።።

እንዲህ ስትሉ ነው ስሙ የገነነው

የፈራው መስሎት አገር የሚያብጠው።።

ዘዴ መላ አታብዙ ጦር ይታዘዝና

በጎይል ተገዶ ይምጣ ይያዝና

እምቢም ካለ ይምጣ ይያዝና

ላንድ ወንበዴ ሽፍታ አይሥጋ መንግሥቱ።።

ራስ ዐሊ

እናቱ ለሚሉት እኔም ነኝ ደጋፊ

መሣሣት አያሻም ለዚህ ለተጋፊ።።

ይገባዋል ለርሱ ጭካኔ እንዳመሉ

መቀመጫ እንዲሆን ላመፀኛ ሁሉ።።

ከመኳንንት አንዱ።።

እኔም ዐውቄዋለሁ ጀግና እኮ ነው ካሣ

ከቶ እንዳይመስላችሁ ሳይቁርጥ የተነሣ።።

አሳቡ ረኻቦም ነው አይደለም የዋዛ

ዐመፀኛ አይደለም ከቶውም ወንበዴ

ከጎይል የተሻለ ሌላ እንፈልግ ዘዴ።።

ቱርክን ያኽል ጠላት በጣም የሚያሠጋ

ሊዋጋን ተነሥቶ ሳለብን አደጋ (*)

እንዴት እርስ በራስ እኛው እንዋጋ።።

በዚያን ጊዜ በቱርክ መሪነት ግብጽና ደርቡሽ በሰሜንና በምሥራቅ (ሐረር) በኢትዮጵያ ላይ የወረራ ሥራ ይዘው ነበርና የጦርነት ጊዜ ነው።።

ካሣን ማስደሰት ነው በጣም ማባበል

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

የመጣን ጠላት እንዲከላከል።

እቴጌ።

ይህን ዐይነት አሳብ እኔ እቃወማለሁ

ፈርታችሁት እንደሁ እኔው እዘምታለሁ።

ደግሞ ላንድ ሽፍታ ይኸን ያክል ጣጣ

እጅግ የሚያስፈራ ጠላትም ቢመጣ

አንለማመጥም አንድ ወንበዴ ሽፍታ።

ፈርተውኛል ብሎ ልቡ ሳይበረታ

ጦር ይታዘዝና በቶሎ ይመታ።

ራስ ዐሊ።

እናቴ የሚሉት ቢሆንም ትክክል

ጉዳት ሳያገኘን ለመጉዳት እንድንችል።

አይከፋም መማከር ማማረጥም ዘዴ

ጠላት አይናቅም ቢሆንም ወንበዴ።

መነሹሴው።

በየአድባራቱ በየባላገሩ

የሚወራው ወሬ ብዙ ነው ነገሩ።

ካሳ የተባለው ሽፍታና አሸባሪ

ጎያል የሚሆን ነው ላልጋውም አስፈሪ።

እርሱ ነው እያሉ ዘውዱን የሚወርስ

ቴዎድሮስ ተብሎ በጎይሉ የሚነግሥ

ይህን እየሰማ አድሮበት ትዕቢት

ልቡ በጣም ኮርቷል በሀሰት ትንቢት።

ይህ የቀን ሕልም ነው መጨበጥ ደመና

በጣም ተጭኖታል ክፉ ድንቁርና።

በጣሙን ይገርማ እንዲህ ያለ ትዕቢት

ወገኛ ነው ለካ ያውም ባለትንቢት።

ከዳዊት ሰሎሞን ቅባት የሌለው ሰው

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ወይም ከመሳፍንት ዘር ውልደት የሌለው

አይቻለውም መንገሥ ምን ሞያ ቢኖረው።

የኢትዮጵያ ታሪክ እርሱ እምቼ አጠና

በጣም ያልበሰለ ጥሬ ሰው ነው ገና።

ሀስት እያወራሁ እኔ ልባል ባይ

የሚያወራለትን አንዳንድ አታላይ

እየሰማ እኮ ነው የያዘው ትዕቢት

እኛን አስለቅቆ ሊሆን ባለቤት።

በጣም ያሳዝናል እንዲህ ያለ ድፍረት

ወሬው መወራቱ ለእኛኮ ነው እፍረት።

ቅባት የሌለው ሰው ለመንገሥ ማሰቡ

እንዴት ቢንቀን ነው ሰነፍ ቢሆን ሕዝቡ።

ይሁን ምን ይደረግ እርሱም ይንጠራራ

ልቡን ያሳብጠው ያድርገው ተራራ

እንደዚህ እያለ ባገሩ ሲያስወራ

ይመስለው ይሆናል እኛም የምንፈራ።

በከንቱ ውዳሴ ልቡ ቢደነድን

ተዋርዶ ከመቅረት ምንም ቢሆን አይድን።

በእንዲህ ያለ ትዕቢት ልቡን የሞላው

ተይዞ ይሰቀል በመጨረሻው።

ይታዘዝ በቶሎ ደጃዝማች ወንድይራድ

ከነሠራዊቱን ገሥግሦ ይሂድ።

፪ኛ ትርኢት።

ደጃች ወንድይራድን አሁን ቶሎ አስጠራው

ትእዛዙን አጥብቀን እኛው እንንገረው።

፪ኛ ትርኢት።

እቴጌ መነን ራስ ዐሊ መኳንንት መነኩሴ ደጃዝማች ወንድይራድ የልፍኝ አሽከር።

እቴጌ ለደጃች ወንድይራድ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ወንድይራድ ወታደርህን ይዘህ ነገ እንድትነሣ

ቢቻል ከነነፍሱ ተይዞ ይምጣ ካሣ።\

እምቢም ካለ ይሙት እንደሚገባው

እዚያው ባገሩ ላይ ተሰቅሎ ሬሳው

ከያለበት መጥቶ ሕዝቡም እንዲያው።

ዐመፅ ላለበት ሰው ይህ ነው መድኅኒቱ

ይሁን መቀመጫ ይታወቅ ጥፋቱ።

ደጃች ወንድይራድ (በመመካት)።

የመቤቴን ትእዛዝ እፈጽመዋለሁ

ለዚህ ለወንበዴ እኔ አሳየዋለሁ።

እኔ አመጣዋለሁ ማርኬ በጎይል፤

አሻፈረኝ ካለም እዚያው ይሞታል።

እንኳን አንድ ሽፍታ ቀማኛ ወንበዴ

ብዙ እመልሳለሁ በጦር በጕራዴ።

እኔ ነኝ ወንድይራድ ታማኝ አሽከርሽ

ያን የኮሶ ሻጭ ልጅ የምቀጣልሽ።

ራስ ዐሊ።

ደጃዝማች ወንድይራድ በጣሙ ተጠንቀቅ

ካሣ ብርቱ ሰው ነው በዋዛ የማይለቅ።

እንዳይመስልህ ላንተ እንደ ሌላው ሽፍታ

ጦር መጣብህ ሲሉት በወሬ እሚፈታ።

በጣም ያስፈልጋል አስልቶ መሄድ

ቀድሞ ማደራጀት የድሉን መንገድ።

(ወንድይራድ በመመካት አነጋገር)።

አይስሙ ጌታዬ ሰው የሚለውን

አያስፈራም ካሣ ይንዛ ጉራውን።

ገና መጣ ሲሉት አገር ጥሎ ይሸሻል

ወይም ካንዱ ደብር ገብቶ ይደውላል።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ምንም ጀግና ቢመስል ቢሆን ቀበጥባጣ

ደፍሮ እኛን ለመውጋት ምን ቢሆን አይቃጣ።

ልክ ሳላገብ አልተወውም እኔ፤

ዓለም በቃኝ ብሎ እስኪሄድ ምናኔ።

በተሻለኝ ነበር አርፌ ብቀመጥ

እያለ እንዲቆጨው ዳግመኛም እንዳይቀብጥ።

እቴጌ (ሳቅ እያሉ)።

እንዳነጋገርህ ሥራህ እንዲቀና

አንጠራጠርም ታማኝ ነህና።

ይህንን ዐውቀን ነው እኛም የመረጥንህ

በጦር ሞያህና በታማኝነትህ።

(ለፍልኝ አሸከር)።

አሳየው እንግዲህ ጥጋቡ እንደማይበጅ

ለደጃች ወንድይራድ አጠጣው ደጎና ጠጅ።

(ወንድይራድ እጅ ይነሣል)።

መጋረጃ።

ክፍል ሁለተኛ።

፩ኛ ትርኢት።

ወይዘሮ ተዋበች ደጃዝማች ካሣ ገብርዬ፥ ዓለሜ ገልሞ ደጃዝማች ካሣ ሰፈር ይመላለሱ።

ደጃች ካሣ።

እግዜር ያለው ላይቀር አንዴ የወሰነው

መሥጋትም መጨነቅ ምንም ጥቅም የለው።

ፍርሃት ምንድር ነች ራሱን ላመነ

ሞት እንዲሁ ከእግዚአብሔር እንደ ተወሰነ

ላዳም ልጆች ሁሉ ነው የማይቀር ዕዳ

አይገባም ከቶ ሊመስለን እንግዳ።

ወይዘሮ ተዋበች።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

እንኳንስ ለወንዱ ቢሆንም ለሴቱ

ታዞለት የለምን የማይቀረው ሞቱ።

ታላቅ ስንፍና ነው ለሰውም ዕፍረእት

ሞትን እየፈሩ መኖር በውርደት።

ገልሞ።

እመቤቴ ያሉት ይገባኛል እኔ፤

አልሞት ባይ ተጋዳይ የለበት ኩነኔ።

ዘላለም በግ መስሎ ከሚገኘው ኑሮ

እንዳንበሳ ሁኖ መሞት ነው ተከብሮ

ደግሞም በውነት ዕድሉን ላወቀው

እንኳንስ ጦርነት ቢሆን ያፈቀደው

ምኞቱን መለወጥ አይገባውም ሰው

እኔ እንደሚመስለኝ ልቤም እንደሚያምነው

ቁራጥነት ያለው ድል አድራጊ እሱ ነው።

ይልቅም አንደኛ ቁርጦ የተነሣ

ክብሩ እንዳይጐድልበት በጣም የሚሣሣ

አይጠረጠርም ድል እንደሚነሳ።

ደጃች ካሣ።

በዚህ ዓለም ካለው ከመልካሙ ነገር

ከሁሉ ይበልጣል መኖር በመከበር

ሁሉ አላፊ ሁኖ ከሞት ጋር ሲቀበር

መልካም ስም ብቻ ነው ለትውልድ የሚቀር።

ገልሞም እንደሚለው ለክብሬ እቆጫለሁ

ስሜን ለማስነሣት አንዴ ቁርጫለሁ።

ኢትዮጵያን ለመግዛት እኔም እመኛለሁ፤

እግዜርም ከኔው ጋር መሆኑን አምናለሁ።

እየደጋገመ ሕልም አሣይቶኛል፤

ቴዎድሮስ የምትባል አንተ ነህ ብሎኛል።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ለኢትዮጵያ አንድነት ተጋደል ተዋጋ፤

ሐሳብህ ሲፈጸም እንድታገኝ ዋጋ።

ለመንግሥቱ መሪ ብርቱ ስለ ጠፋ

ቱርክ ከያለበት መጥቷል እየገፋ።

ኢትዮጵያን እግዜር በጣም ይወዳታል

አንተ መሪ እንድትሆን አስቦ ሰጥቷታል።

እንደዚህ እያለ መልአኩ ሲነግረኝ

የነገሩ አመጣጥ በጣም አስገረመኝ።

(ብድግ ብሎ በኃይል አነጋገር)።

እንግዲህ እኔ ነኝ የእግዜር መልክተኛ

ትእዛዙን ሳልፈጽም እንቅልፍ የማልተኛ።

ራስ ዐሊ ሲንቁኝ ድኻ ነው እያሉ

ተንቁ እንደማልቀር ወደ ፊት ያያሉ።

ይመስለዋል ለርሱ እንዲህ የሚዘልቅ!

ሙያ ሳያሳዩ እንዲያው መንደላቀው።!!

ገብርዬ።

አሁን ያልከው ሁሉ በጣም ትክክል ነው

እኛም ዕድልህን ቁይቷል ካመነው።

ስማኝ የኔ ካሣ አድምጠኝ ጌታዬ

የልቤን ልናገር ላንተ ላልኝታዬ።

ትሆናለህ መሪ ለመላው ኢትዮጵያ

ለጦበዞች ሁሉ አንተ ነህ አርአያ

ለኢትዮጵያ ጀግኖች የዘላለም መኩሪያ።

መልክህ የሰው ቢሆን ልብህ ነው ያንበሳ

ፈረስህም ጉበዝ ታጠቅ ነው መይሳ

ስምህም ይሆናል ላገር መከበሪያ

ለጉበዝ ለጀግና ምሳሌ መጠሪያ።

ግፋበት ጌታዬ ግንባርክን አትጠፍ

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ተሰጥቶሃልና ዕድልክን አትለፍ።

ዳዊኢት ጐልያድን ሲገጥመው በድፍረት

ሕዝቡን ለማውጣት ነው ከክፉ ባርነት።

አንተም ለኢትዮጵያ ካሣ እንድትሆንላት

ቀብቶሃል እግዜር የለብህም ሥጋት።

ታሪክ ዐዋቂና የሚለው ንግርቱ

ካሣ ቴዎድሮስ ሆኖ ይመራል መንግሥቱ።

ስምህ ለዘለዓለም ከቶ የማይረሣ

ትበላለህ ቴዎድሮስ ዕጓለ አንበሳ።

እንግዲህ በከንቱ ጊዜህን አታጥፋ

ዕጣችን አንተ ነህ ወደ ፊት እንግፋ።

ቅድሙንም ቢሆን ብላሃለች ታጠቅ

ማመንታት አያሻም መንፈስህ ይጠንቀቅ።

ቋራ ላይ የበራው የሰደድ እሳት

ለትግሬ ላማራ ይሆናል መብራት።

(በኃይል አነጋገር)።

በል ምራን እንድሂድ በድል ወደ ክብር

ካንተ ጋራ ለመሞት ገብተናል እድር።

ያገራችን ጠላት መክረው ተማምለው

በየጠረፉ ላይ ሲሰለፉ ተማምለው

በሰምሜን በምሥራቅ ሲሰማ ድምፃቸው

መይሳው ካሣ ነው የሚበትናቸው።!!

ሰው ሐሳቡን ቁርጦ ዐላማ ካበጀ

የሚያግደው የለም ልቡ ከደረጀ።

እኔ ነኝ ገብርዬ ይሽንን የምልህ

እስከ ዕለተ ሞቴ የማልለይህ።!

ደጃች ካሣ።

ገብርዬ ነገርህ ለልቤ ተሰምቷል

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ክብርን ለመከተል ልቦናዬ ቁርጧል
እውነትም እንዳለከው እግዜር ያለው ላይቀር
ማመንታትን ትቶ መታገል ነው ላገር።
ምኞቴ ሰፊ ነው አንተ እንደምታውቀው
ለኢትዮጵያ አንድነት ላገሬ ልማት ነው።
ወንዶቹ ተቀምጠው ሴቶቹ ሲነግሡ
ደርቡሾች በኛ ላይ ሊዘምቱ ተነሡ።
(ተእንሥቶ እየተንጐራደደ)።
የነአብርሃም አጽብሓ የካሌብ አገር
እንዴት በቁማችን በደርቡሽ ትወረር?
የጐንደር ጐበዞች ወዴት ደረሳችሁ
የሸዋስ ጐበዞች ምን አስነፋችሁ፤
የትግሬስ ጐበዞች ማነው ያስተኛችሁ
አውራ ብታጡ ነው ኑማ እኔ ልምራችሁ።
ባንድነት ሰብስቤ አውራጆቹን ሁሉ
እንድትተባበር ኢትዮጵያ በመሉ።
ሕግ ደንብ አውጥቼ ሕዝቡንም ሳልበድል
ተፈርተን ተከብረን እንድንመሰገን
ስንፈት ፍርሃትን ተንኮልንም ትተን
ባንድ አሳብ ተመርተን ብርታት ከተመላን
ለመጪው ትውልዶች ክብር እናስገኛለን።
ነፍሮች ያገኙትን ጥበብና ዕውቀት
የልጅ ልጆቻችን እንዲራቀቁበት።
ያንድነትን ጉዳይ እኛው አደራጅተን
ጠረፍን ፀጥ አርገን አጥርም አበጅተን
ለኋላ ብናቁይ ታላቅ ኢትዮጵያ
ይሆንልን ነበር የዘለዓለም ሞያ።
እነዚያም ልጆቹ ኋላ የሚመጡት

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ጥበብን አግኝተው በዘዴ እሚሠሩት

ተከብረው ለመኖር ምንም አይሳናቸው

እኛ ያቀድነውን ሲያውቅ ልቦናችው።

ብልሆች ንጉሦች አገር የሚያኮሩ

ከጐንደር ቢጠፉ ከሸዋ ከሥሩ

ይነግሡ ይሆናል ከእኔም የሚፈሩ።

ከትግሬም ይገኛል ሃይማኖት አጥባቂ

ጠረፍ አስከባሪ ጠላት አስጨናቂ። (*)

እግዜር ነው የላከኝ ለኢትዮጵያ አብነት

ባንድ ሕግ አግብቼ ላኖራት ባንድነት።

*አፄ ዮሐንስ

(በኃይል አነጋገር)።

ቃሌን የማይሰማ ውጉዝ አርዮስ ነው!!

በካራና በሴፍ በእሳትም ጠፊ ነው!!

የጐንደር የጐጃምሃ የትግሬ ሕዝብ ሁሉ

የሸዋ የወሎ እስላም ክርስቲያኑ አረመኔው ቅሉ።!

እኔ ነኝ ገሸርያችሁ እግዜር የመረጠኝ።!

ርኅራኄ የማላውቅ ምሕረትም የለኝ።!

ሜዳውን ፈፋውን ዳገቱን ሮጬ

እኔ እመራዋለሁ መንገዱን መርጬ።!

እኔ እገዛዋለሁ ራሱን ረግጬ።!!

ገልሞ (ወጣ ብሎ ተመልሶ ይገባል)።

ፈረሰኛ መጥቷል ወሬ የሚሰጠን

እስቲ ይቅረብና አሳቡን ይንገረን።

ካሣ።

አስጠራው ቶሎ በል የሚለውን ልስማው

ከጐንደር ይሆናል ተልኮ የመጣው።

መልዕክተኛው።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ከጐንደር ተልኬ ስገሠግሥ ደረስኩ
ሌቱንና ቀኑን እንዳውሬ እየሮጥኩ
የጐንደር ከተማ መላው ሲናገር
እጅጋን ለመያዝ እነሆ ጦር ታዟል
ደጃዝማች ወንድይራድ በፉከራ መጥቷል።
የቋራውን ሸፍታ አመጣለሁ ብሎ
በታማኝነቱ ተገዝቶ ምሎ።
እስኪ ጥቂት ቀናት እዚሁ ይደርሳል
አሁኑን ዘዴውን ማደራጀት ያሻል
ብለህ ንገር ብለው አባ ልከውኛል፤
ብዙዎችም ጀግኖች አደራ ብለውኛል።

ካሣ።

ጭምጭምታውን እንኳን ቀድመን ሰምተነዋል
የላከህ መልካም ነው ምስጋና ይገባዋል።
ወንድይራድ ቢመጣ ሲሳደብ ቢዝት
ከቶም ራስ ዐሊ ቢመጡ ንግሥት
የቋራው አንበሳ የለውም ሥጋት።
እግዜር ያለው ላይቀር እንዴት የጻፈው
በከንቱ ይሠጋል ይጨነቃል ሰው።
ተው ዝም በለው ይምጣ ይሁን እንዳሻው፤
ፊቱ አይመልስም ካሣ መይሳው።

ግልሞ።

ወንድይራድ ቢፎክር ቢሰማ ዛቻው
አያስፈራም ለኛ የርሱ ዘመቻው።
እግዜርን ታምነን ሁል ጊዜ በቅን
እንገጥመዋለን ሌትም ቢሆን ቀን።
ድል ለተጻፈለት አንዴ ለቀባው
ማንም አያግደው እስኪደርስ ቦታው።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

አሁንም እቴጌ በከንቱ ይደክማሉ

ድሉን ላያገኙ እንዲያው ይንገላሉ።

ገብርዬ።

መቼም በነርሱ ቤት እኛ ደካሞች ነን

ላንድ ሽፍታ አይሰጡም እቴጌይቱ መነን።

አንተ እንደምትለው ልባችንን ቢያውቁት

በቃኝ ዓለም ብለው አልጋውን በሰጡት።

ዓለሜ።

ጠላት እንዳይደፍረን እንዳይዘን ባዕድ

ሰላም እንድትገኝ ለመጪው ትውልድ።

የሚገዛት ይሻል ኢትዮጵያን ጠቅሎ

ትጌቴን ማን ይምከር ተው አይሆንም ብሎ።

ወ/ሮ ተዋበች።

እንኳንስ እንደኛ ገና ላልታወቀው

አለቅለት ይሏል ጃኖ ለለበሰው።

ስለዚህ በእቴጌ መፍረድ ያስቸግራል

እንዲያው ለወጉ እንኳ ቢዋጉ ይሻላል።

ገልሞ።

እረ እንዳይመስላቸው እኛን የገመቱን

ወንድይራድስ ቢሆን መቼ አሰበ ሞቱን።

እየተሳደበ እንደዚህ መምጣቱ

ጎይል ቢሰማው ነው ቢመካ መንግሥቱ።

እኛም አንታተለል እንሁን ጥንቁቅ

አይገባም ከቶ ጠላትን መናቅ

እነሱም ይመኩ በገዛ ኃይላቸው

እኛም ሃይማኖትን ልብ እናሳያቸው።

መጋረጃ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

፪ኛ ትርኢት

ደጃዝማች ካሣ ወታደሮቻቸውን ይጐበኛሉ።

ካሣ።

አንተ ማነህ?

ባቋቋምህ ሁሉ ጐበዝ ትመስላለህ።

ወታደር።

አዎን ጀግና ነበርኩ በረሃ የለመድሁ

ዝናህን ሰምቼ ልከተልህ መጣሁ።

ካሣ።

ይኸኛውስ ማነው?

ቦታው ጠፍቶብኛል ወዴት ነው የማውቀው።?

ወታደር።

ጊዜው አያሌ ነው ጌታዬ ሲያውቁኝ

ከቋራ ስንወጣ ጋሜ ነበርኩኝ።

በክፉም በደጉም ከርስዎ አልተለየሁ

ታማኝ አሽክርዎ እኔ ነኝ ገበየሁ።

ካሣ።

ስሙኝ አርበኞቼ በኔ እምነት ያላችሁ

ተስፋችሁን ሁሉ በኔ ላይ የጣላችሁ።

ልባችሁ ከፍ ይበል እኔ ነኝ መሪያችሁ፡

ሲጠራ ይኖራል ከኔ ጋር ስማችሁ።

(ካሣ ሁሉንም እየዞሩ ካስተዋሉ በኋላ ከፍ ባለ ቦታ ቆመው ጦራቸውን ተመርኩዘው ይናገራሉ)።

ሃይማኖትን ይዘን ለኢትዮጵያ አንድነት

ለታዘዝነው ሥራ እንድከምን በውነት።

ሞትና መናቅ ያሻል ክብርን ለማግኘት

አለመንጓት ነው ለከንቱ ሕይወት።

ልባችሁ ከፀና ካላችሁም እምነት

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

አስገኛችኋለሁ የማያልፍ ክብረት።

ኢትዮጵያስ እንድትሆን ዘለዓለም ተፈሪ

እኔ እሆናታለሁ ጎይልና አስከባሪ።

ሕግ ደንብ አውጥቼ በደንብ አሳዳሪ

እግዚአብሔር መረጠኝ ለርሷ አስተናባሪ።

ወየው ላልተረዱት ለሚቃወሙኝ

ይሻላቸው ነበረ አሁን ቢያደምጡኝ።

በከንቱ ይለፋሉ መንገዴን ለማጠር።

አምላክ የመረጠኝ ቅድሙን ስፈጠር።

አሳቤ ስኑ ነው ምን ጊዜም አይበገር

እንቅልፍም አይወስደኝ አንድ እስኪሆን አገር።

ከሕንድ ውቅያኖስ እስከ ኤርትራ ባሕር

የቀድሞ ነገሥታት ያቀኑትን ሁሉ

ሰብስቤ ባንድ ዘውድ እንዲቀላቀሉ

መታገል መጋደል አናገኝም ፋታ

በገደል በሜዳው ውጊያ ጧት ማታ።

ለዚህ ዐይነት ኑሮ ቁርጠን ተነሥተናል

የመረጠኝ አምላክ ሁል ጊዜ ይረዳናል።

ኃይለኛ ለመሆን ድልን ለማግኘት

በጣም ያስፈልጋል ጽኑ ሃይማኖት።

ራስንም አምኖ ልቡናን ማጽናት

በገፆመሩት አሳብ መቀጠል በምነት።

ያርበኞች ተግባር ነው የሚሞቱበት።

እምነትና ተስፋ በኔ ላይ ጥላችሁ

አደርሳችኋለሁ አይጠፉም ስማችሁ

እስከ መጨረሻው ከኔ ጋር ካላችሁ።

ፈተናው ብዙ ነው ትግላችን ጠንካራ

ሜዳ ወንዝ ማለፍ መውጣትም ተራራ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ኢትዮጵያ አንድ ሆና በኛ እስክትመራ
ብዙ ድካም አለ እስኪያልፍ መከራ።
በጐጃም በትግራ በሸዋ በጐንደር
እንሄዳለን ጐብዝ ሕዝብን ለማስገበር።
አንድነት ተፈጥሮ ሁሉም ሲተባበር
ጎይል እናገኛለን ቱርክን ለማባረር።
ባንድ ሃይማኖት ሁነን ሰላምን ስናገኝ
ትዳር እንዲቃና ሀብትም እንድትገኝ
ላገር የሚጠቅም ብዙ አሳብ አለኝ።
አሳቤ እንዲፈጸም ወይ እግዚአብሔር ስመኝ
እኔስ እሰጋለሁ ሰይጣን እንዳይመቀኝ።
ድንቁርና በዝቶ ክፋት ካሸነፈ
ተቃዋሚ በዝቶ ሕዝቡም ከሰነፈ
ክብሬን ሳላሳንስ መሞት ይሻለኛል
ድካምና አሳቤን ትውልድ ያውቅልኛል
ምኞቴንም ሌሎች ይፈጽሙልኛል።
ገብርዬ።
ዕድልህን በማመን ኮከብህን አይተን
መጣን ከያለንበት ጀግኖች ለመሆን።
እኛ እንደምንወድህ አንተም ካመንክን
መሪያችን እንተነህ ማንም አይነካህ።
እዘዝ ዝግጁ ነህ ቃልህን ለመፈጸም
ላገር ለክብር ነው የምናፈሰው ደም።
እንሂድ እንብለው በሴፍ በጐራዴ!
ተብለን አንቀርም የቋራ ወንበዴ።
አሁን ይረዱታል መሆኑን የዋዛ
ካሣ ቴዎድሮስ ሆኖ ሁሉንም ሲገዛ።!!
ሦስት መልክተኞች ይደርሳሉ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ካሣ።

ደጃዝማች ወንድይራድ የት ደረሰ ይላሉ?

ጦሩስ ምን ያክል ነው እረ ለመሆኑ።?

፩ኛ መልክተኛ።

እንዳካሄዳቸው እንደ ገመትነው

እስከ ሁለት ቀን የሚደርስ ነው።

ጦሩም አያሌ ነው መሣሪያም አብዝቷል።

ደጃዝማች ወንድይራድ በጣሙን ይዝታል።

«ይህንን ወንበዴ አባቱ ያልቀጣው

«እጅን ጐትቼ ነው እኔ የማመጣው።

«ደርሶ ላንድ ሽፍታ ይህን ያህል ዋጋ

«አነሰው ወይም ለሱ ካሽከሮቹ ቢዋጋ።

ይሻለው በነበር አርፎ ቢቀመጥ

ከናቱ ጋር ሆኖ ኮሶ መሸምጠጥ።

እንደዚህ እያለ የሰው ስም ያጠፋል

አዝማሪ አቁሞ ብዙ ይለፈልፋል።

ካሣ።

ሕዝቡስ ምን ይለኛል ከተማው መንደሩ፡?

፪ኛ መልክተኛ።

ከተማውም ሆነ መላው በጌምድሩ

ካህናቱም ቢሆን ሕዝቡ ባላገሩ

የሚመካከረው ብዙ ነው ነገሩ።

ንግርት አለ እያለ ነቅቷል ወታደሩ።

መቼም ወታደሮች ጀግና ይወዳሉ

ቴዎድሮስ የሚባለው እሱ ነው እያሉ

እርስ በራሳቸው ይንሾካሾካሉ።

ንግስቲቱም ቢሆን ይህንን ሰምተው

እዘምታለው ብለው ቁርጠው ተነሥተው።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ራስ ዐሊም ከተው ለጦር ሲመቻቹ

ወንድይራድ ይበቃል አሉ መካሮቹ።።

ገብርዬ።።

እንግዲህ ከመጡ እኛም ቦታ እንያዝ

ቃፊዎች ይድፈጡ ካፋፍና ከወንዝ።።

ካሣ።።

የሁለት ቀን መንገድ ግና ከቀራቸው

ወደኛ ሲመጡ እኛ እንድሂድባቸው።።!

ያን ተረተር አልፈን ከሜዳአው ስንደርስ

በካራና በጦር በእግርም በፈረስ

እንገጥማቸዋለን ግምባር ለግንባር

እንዲያጠኑ ከኛ የጦርን ተግባር።።

መጋረጃ።።

፫ኛ ትርኢት።።

ካሣና ተዋበች (ካሣ ከውጭ ይገባል)።።

ካሣ።።

ደኅና ሁኝ ተዋበች በጸሎትሽ እርጂኝ

አያትሽ ጦር ልከው ፈለጉ ሊወጉኝ።።

ቅድሙንም ቢሆን እኔን አልወደዱኝ

ምን ይሆን ምክንያቱ እንደዚህ የጠሉኝ፡?

ተዋበች።።

ምክንያቱንማ አንተስ መች አጣኸው

በሞያህ በዕድልህ ተመቅኝተውህ ነው።።

አባቴም ከርሳቸው ምቼም አይለዩ

ልባቸው አያርፍም ያንተን ሞት ካላዩ።።

ግን እኔ እማስበው በጣሙን የማዝነው

እይሰጠኝን ዕድል በማመዛዘን ነው።።

ባንድ ፊት አባቴ ባንደኛው ለባሌ ብዙ ነው ኀዘኔ።።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

የሁለታችሁ ጠብ መከራ ነው ለኔ።

ያንዳችሁ ማሸነፍ ጎዘን ይሆነኛል

ይህን ሁሉ ሳላይ ብሞት ይሻለኛል።

ካሣ።

ተዋበች ታውቂያለሽ እኔ እንደምወድሽ

በውነት ከልቤ ነው አሁን የምወቅስሽ

በጣም መገፋቴን ልብሽ እያወቀው

የምታመነች ላባት አድልተሽ ነው።

ታጠቅ ብለሸኝ ነው የተነሣሁት

ይኸው ታጥቂያለሁ ገድዬ ልሞት።

እንዳይመስልህ አንተ አሳቤን የለወጥኩ

ላባቴ ሳስቼ ውርደት የመረጥኩት።

አንተም ታውቀዋለህ የሴት ሆድ ቡቡ ነው

አይችልም ሊጸና አንዴ በቁረጠው።

ስለዚህም እኔ በፊት ቀሰቀስኩህ

ራሴ መልሼ አታሸንፍ አልኩህ

ምናባቴ ላድርግ ግራ ቢገባኝ ነው

ለወዶች ብቻ ነው መቁረጥ የተሰጠው።

ካሣ።

ለኔም ይሰማኛል ይኸ ሥጋትሽ

ካባት ከዘመድሽ ሲዋጋ ባልሽ።

እንኳንስ ለሴቶች ያስቸግራል ለወንድ

በቁረጡት አሳብ መሄድ ባንድ መንገድ።

ብርታት ያስፈልጋል መሆን እንደ ብረት

ምኞት እስኪፈጸም መታገል መቃተት።

አንቺም ታውቂዋለሽ የልቤን ምኞት

አንቺ ትቀሪያለሽ ለዘርሽ አሥራት

እቴጌ ተዋበች ያባ ታጠቅ ሚስት

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

በባልዋ የምትወርስ ያባትዋን መንግሥት።

ተዋበች።

ድኻ ነው በማለት ንቀት ስላሳዩህ

በጣም ተቁጭቼ ታጠቅ ተነሥ አልኩህ።

አባቴን ነቅፌ አንተን መከተሌ

ልቤ ቢነግረኝ ነው መሆንኽን ዕድሌ።

ሆኖም ምን ብወድህ በጣም ብቁጭልህ!

የልቤን መጨነቅ ምንም አልሰውርህ።

ካሣ።

ምንድርነው ጭንቀቱ ከቁረጠ ልብሽ

ክብር ለማግኘት ነው የሚዋጋ ባልሽ።

በእውነት ልንገርሽ አድምጪኝ ተዋበች

ቁርጠን ተነሥተናል እንግዲህ አታመንች።

ይገባኛል ብሎ ትግል የገፐመረ

ተበደልኩም ብሎ የተከራከረ

አይገባውም ከቶ ከመንገድ መመለስ

ስንፍና አስገብቶ መንፈስን ማለስለስ።

ቀርጠኛውን አሳብ አጥብቆ መከተል

ፈተናውን ሁሉ ጨክኖ መቀበል።

ይህ ነው ሕግጋቱ የሰው ልጅ ተግባሩ

ፈተናውን ሲያልፈው እንዲታወቅ ክብሩ።

ሁለት ወዶ አይሆንም ለቀጥታ ኑሮ

ከንቱን መናቅ ያሻል ለመኖር ተከብሮ።

በቁረጡት አሳብ ይሉኝታን ካስገቡት

ልብን ሰውነትን ምክር ከጠየቁት።

ዘዴ ምክር ትዕግሥት ፍርሃትም ደግሞ

መንፈስን ሲወሩት ይወድቃል ተዳክሞ።

ስለዚህም እኛ ቁርጠን በሚገባ

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ማመንታት፤ ከንቱ ነው ሆድሽ እንዳይባባ።

ተዋበች።

አንተ እንደምትለው ሆዳችን ቢቁርጥም

ያጋጣሚው ክፋት መስማቱ አይቀርም።

ጥቅምን ሆነ ክብርን አንዱን ከፈቀዱት

ያንደኛውን መንገድ መርጠው ቢከተሉት።

ይሉኝታን ጨምሮ ልብን ካልመከሩት

ስሜትን ምኞትን በምን ይመጥኑት።

ማናቸውም ነገር መጠን ከሌለበት

ምንም መልካም ቢሆን ሚዛን ካልገባበት

የሰው ሥራ ሁሉ መንቀፍ አለበት።

ስለዚህም ልብን ቢሰሙት አይከፋም

ልብን ያዳመጠ ሰውነት አያጣም።

ልቤ ተሸብሮ በዕድሌ ቢያዝንበት

ስንፍና ነው ብለህ አንተ አትፍረድበት።

ጎዘኔ ላባቴ ላንተም ለባሌ ነው

በንዲህ ያለው ዕድል እንዴት ደስ ይበለው።

ከማንም አብልጬ እኔ እንደምወድህ

አትጠራጠርም ይረዳዋል ልብህ።

ካሣ (በትካዜ)።

እኔም ቅሬታዬን ባፌ ብሰውረው

ስሜቱን ጨቁኜ አልሰማህም ብለው።

ምን እንኳን ብጨክን ባስገድደው ልቤን

ማሰቤኮ አልቀረም የምወዳት ሚስቴን።

በገደል በጫካው ስኖር በሸፍትነት

ነፃ ጎበዝ ሆኜ ስሂድ በያለበት

በልቤ ሳልሠጋ አሳብ ሳይገባበት

አንቺን ካወቅሁ ወዲህ ልቤን ገባው ስንፈት።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ሞትና መከራን ማሰብ ዝምሬያለሁ

ካንቺ እንዳልነጠል ውስጡን እሰጋለሁ።

ይህ ከንቱ ስንፍና በልቤ ካደረ

በፈቃዴ ብቻ መመራቴ ቀረ።

ተዋበች።

ፍቅር የሚባለው እንዲህ የሚያስጨንቅ

ከሰው ስሜት ሁሉ ሁል ጊዜም እሚልቅ።

ልብ ላለው ሁሉ የማይቀር ዕዳ ነው።

ማነው ሰው የሆነ እሱን ያላወቀ

ለሚወደው ሰግቶ ልቡ ያልተጨነቀ።

ሊገባው አይችልም የፍቅር ስሚቱ።

ድካምና ልፋት ሆኖበት ሕይወቱ

ደስታን ሳያውቃት ይደርሳል ከሞቱ።

ካሣ።

ፍቅር ለሰው ልጆች ቢሆንም መሪያቸው

ጀብዱ ሙያና ጽድቅ ታምር ቢያሠራቸው።

ከቶ ምን ቢጸና ስሜቱም ቢያይል

ተግባርን ሊያስረሳ ምን ቢሆን አይችል።

ስለዚህም እኛ ምንም ብንዋደድ

ክብራንች እንዲድን ልባችን ይገደድ።

ደኅና ሁኝ ተዋበች የልቤ ወዳጅ

ሥጋት አሳብ ትተሽ ደስታን አዘጋጅ። (ትቷት ይሂዳል)።

ተዋበች (ብቻዋን በትካዜ አነጋገር)።

ከዚህ ከፊተና ከልብ ሥቃይ

ምንቸገረው ነበር ፀሐይን ባላይ።

ያኔ ተማርኬ ቱርክ ሲወስደኝ

ካሣን እግዜር ልኮ ለምን አዳነኝ (*)

*ራስ ዐሊ ከግብጾች ጋራ ሲዋጉ ወይዘሮ ተዋበች ተማርከው ሙሳፓሻ የሚባለው የጦር አዝማች ሊወስዳቸው ሳለ ራሳቸውን በመርዘኛ ጩቤ ወግተው ሊሞቱ ተዳርሰው ደኛች ካሣ

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ምንም ሽፍታ ቢሆኑም ካገራቸው ጠላት ጋራ ይዋጉ ነበርና ማታውን በግብጾች ሰፈር ላይ አደጋ ጥለው ወይዘሮ ተዋበችንም የተወጉትንም መርስዝ ደሙን መጥጠው አድነዋቸው ከዚያ በኋላ ተጋቡ ይባላል።

ሞቼ ተረስቼ መና ሆኜ ብቀር

ከዚህ ከፈተና ባልደረስኩም ነበር።

አዬ ጉድ ሴት መሆን ደካማ ፍጥረት

ልቤኮ ስሜቴን መቻል አቅቶት።

ሲሸበር ሲዋልል በከንቱ ስንፈት

ወንዱንም ሞክረው ሊያስተምረው ፍርሃት።

እሱስ በእውነት እንዴት ይታዘበኝ

እንዲህ ሳመነታ እንዴት ይገምተኝ።

ተነሥ ታጠቅ ብዬ አስቁጭቼ ልቡን

ደግሞ እኔው መልሼ አስቁጭቼ ልቡን

ደግሞ እኔው መልሼ ላስለውጥ አሳቡን።

ጎዘኔን ፍርሃቴን ገልጬ ነገርኩት

ይሉኝታ ሰውነት እያልኩ አባባሁት።

ገረድ (ንግግርዋን ታዳምጥ የነበረች)።

እመቤቴ አይዘኑ እንደዚህ አምርረው

ልብዎ ቢባባ ከቶ ነውር የለው።

ላባቱ ለባሉ የማይሣሣ ማነው?

የነገሩ አካኋን ሲታሰብ በውነቱ

ልብዎ ቢሠጋ ቢጨነቅ ላባቱ

ምን ክፋት አለበት ምንድርነው ጥፋቱ።

ይልቅስ ልንገርዎ እውነተኛ ነገር

ባልዎ ሸፍቶ ሲበጠብጥ አገር

እንደዚህ ሲሠራ ተው ብለው ቢመክሩት

መልካም አረጉ እንጂ ምንድርነው ያጠፉት።

ይልቅስ በውነቱ የሚያስወቅስዎ

ለባልዎ አድልተው ሲጣሉ ካባትዎ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ተዋበች (በቀጣ አነጋገር)።

እመቴ ደፋር ነሽ ምላስሽ ረዝሞ!

እንዲህ ከመናገር ምነው ብትይ ዝም።

ቅድሙን ከጧቱ ባሌን መርጫለሁ

ዕድልህ ዕድሌ ብዬው መጥቻለሁ።

እስከ መጨረሻው እከተለዋለሁ።

ገረድ።

ሆኖም ካባትዎ ባልዎን ሲዋጋ

ባልን ሲከተሉ ይወቅስኂል ሥጋ።

ተዋበች።

ሥጋን ካደመጡት ልብንም ካባቡት

ምን ቢሆን አይቻል ለመድረስ ካሰቡት።

ለሰው ልጅ ዕድሉን ለይቶ ሲሰጠው

ራሱ መርምሮ ዐውቆ ካልገመተው

ዕድልም መከራም የተያያዘ ነው።

በመከራችን ላይ ዕድል አይታጣበት

በዕድላችን ደግሞ እንድከን አይጠፋበት።

ዕድል ብለን ያልነው ኂላ ይቁጨናል።

መከራ እሚመስለው ዕድል ይሆነናል

ዐላማውን ዐውቆ ካልቁረጠ ልቡ

በጣም ያስቸግራል ለመድረስ ከግቡ።

ገረድ።

ልብዎም ቢጨክን ቢጸና አሳብዎ

የሚገባ አይደለም መራቅ ካባትዎ።

በባል ከሚገኘው ማዕርግ ክብርዎ

ይበልጥ የለምን ያለው በዝርቆ።?

ተዋበች።

ካባት ያገኘሁት ክብርና ማዕርግ

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

በርግጥ ይረዳኛል ልቤን ከፍ እንዳደርግ።

ይመክረዋል በጣም እንዲያስብ ወደ ላይ

ክብር እንዳትለየው ውርደትን እንዳያይ።

ስለዚህ ያባት ክብር የዘርም ምስጋና

ልብን እያኮራ ክብርንም ቢያስጠና

ያስገድዳል እንጂ ምቹ ይበቃል ዝና።

ዘር ውልደትን ቁጥሮ ባባት ቢመኩበት

አያስመሰግንም ሞያ ካልሠሩበት።

ከትንሽ ተወልዶ ክብርን የጨበጠ

በምግባር በሥራ በሞያ የበለጠ።

ባላባት ይሆናል በገዛ ምግባሩ

ከፍ ያለ ዋጋ አለው መሠረት ክብሩ።

መጋረጃ።

ክፍል ሦስተኛ

፩ኛ ትርኢት

(የወንድይራድና የካሳ ወታደሮች ሲሸልሉና ሲፎክሩ ይሰማል የወንድይራድ ወገኖች አይታዩም ድምፃቸውና ነጋሪቱ እንቢላው ሽለላው በሩቅ ይሰማል)።

የወንድይራድ ሽላይ።

ያመፀኛ ጠላት አባ ደፋር ወንዴ

አንገቱን ቁራርጠው በሴፍ በጐራዴ።

ካሣ (ለሽላይ)።

እንኳንስ ደጃዝማች ቢመጣም ራሱ

አይታገድ ካሣ ተነሥቷል ፈረሱ።

የወንድይራድ ወገን።

ይሻልሃል ካሣ ኋላ ከመጸጸት

አቅምህን ገምተህ ብትጠይቅ ምሕረት።

የካሣ ወገን።

እያንገራበደ ቢያሰማ ጩኸቱን

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ቁርጧል አንዴ ካሣ አይመልስም ፊቱን።

የወንድይራድ ወገን።

በለው በጠመንጣ በጉራዴም በለው

ይገባዋል ቅጣት እንዲህ የቀበጠው።

የካሣ ወገን።

ወንድ ከቁረጠ ከበዛ ምራቱ

የሚያግደው የለም አይበርድም ንዴቱ።

(የደጃዝማች ወንድይራድ ነጋሪት ይሰማል ፈረስ ሲያስካካና እንቢልታም ፉከራም ይሰማል)።

(የደጃዝማች ወንድይራድ መልክተኛ ራቅ ብሎ ይናገራል)።

መልክተኛ።

እጃችሁን ስጡ በከንቱ እንዳታልቁ

መንግሥት አምሪ ነው ይቅርታ ጠይቁ

ይላሉ ደጃዝማች መልሱን ቶሎ አስታውቁ።

(የካሣ ወታደሮች ይስቁበታል)።

ካሣ።

እንኳንስ ወንድይራድ ቢመጡ ንግሥት

ይቅርታ አንጠይቅም ቢመጣብን ሞት።

ይልቅስ ንገረው ለደጃች ወንድይራድ

ለስብድ አይደለም ጎበዝ የሚዋረድ።

ትምክትም ከንቱ ነው ልቡን ላመነው

ቶሎ እንግጠምና ልኩን ይወቀው።

መጋረጃ።

፪ኛ ትርኢት።

(ካሣ ከጥላ ሥር ተቀምጧል ባንድ ፊት ምርኮኞቹ ባንድ ፊት ወታደሮቹ ቁመዋል ደጃች ወንድይራድ ተይዞ ይመጣል የካሣ አሽከሮች ይፎክራሉ የማረቱትንም ሁሉ ከፊቱ ያስቀምጣሉ)።

ካሣ።

(በመውቀስና በማፌዝ)።

ከሴቶች ጋር ሆኖ መሳደብ መፎከር

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ድልን ሳያገኙ መመካት መወጠር

ከውርደት ያደርሳል በጣምም ከማፈር።

ጀግናን ጀግና አውቆት ሲል እንወዳደር

አይገባም ከቶ ጸያፍን መናገር።

እናቴን ጨምረህ አንተ የምትሰድበኝ

ያዋረድህ መስሎህ ድንጉት የምታገኝ።

እኔ ግን አላፍርም ድኻ ነው ትውልዴ

ድኽነት ይዞኝ ነው የቁረጠው ሆዴ።

በኮሶ ያደገው መሪር ነው መንፈሴ

ችግርን ሳታውቁት እናንተ ፈሰሴ።

ድኻ እያላችሁ ሰውን የምትንቁ (*)

ደርሶ ስትመኩ ስትንደላቀቁ

ጌትነት አይዘልቅም በድኻ ከሳቁ።

*ከቤተ መንግሥት ገብተው በነበረ ጊዜ መኳንንቱ ያደረጉባቸውን ሐሜትና ያሳዩዋቸወን ንቀት በማስታወስ ነው።

(ብድግን ይላል)።

እኔም እኮራለሁ በገዛ ድኽነቴ

ግን ተሰድባ አትቀርም ያች ደኃ እናቴ።

አንተም ለጥጋብህ እንዲሆን ትምህርት

በቃህ አልኩህ ድረስ ማታና ጥዋት

ትጠጣለህ ኮሶ መልካም መድኀኒት

ጥቂት እንዲቀንስ የልብህ ትዕቢት

ካሣ።

(እየተንጐራደደ ለወታደሮች)።

ጎሽ እንዳልላችሁ አሁን ከጥዋቱ

የምንወጣው ብዙ ወደ ፊት ዳገቱ።

ቢሆንም የዛሬው የሚያስመሰግን ነው

አንድ ለመቶ ነው እኛ የገጠምነው።

ምርኮኛው ይቁጠር እራሳም ቅበሩ

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

እግዚአብሔር ይመስገን ንሴብሕ ለክብሩ።

(ለምርኮኞቹ)።

እናንት ወታደሮች ስሙኝ ልንገራችሁ

እኔን እንድትወጉ በትእዛዝ መጥታችሁ

የሎሌነት ተግባር ፈጸማችሁ ከልብ

ቂምም በናንት የለኝ በቀልም አላስብ።

አውቃለሁ ወታደር መታዘዝ ግብራችሁ

ቀኙ ለኛ ሆኖ ከተማረካችሁ

እኔን ተከተሉኝ ልምራችሁ ወደ ድል

አሳያችኋለሁ እንደሚኖር በዕድል።

(ወታደሮቹ እሺ እሺ ይላሉ)።

ካሣ (ለገብርዬ)።

በል ገብርዬ እያየህ ስንቅም አድላቸው

መሣሪያቸውንም መልሰህ ስጣቸው።

የቆሰሉትንም ሰፈር ውሰዷቸ።

ለእረፍትም ጊዜ የለ አሁን እንነሣ

ራስ ዐሊ አለበት ከተፍ እንዳንበሳ።

ድንጋጤው ሳይለቀው ሳይዘራ እሱ ነፍስ

ዐሊን እናጣድፈው እንደ አውሎ ነፋስ።

ደግሞም እንበራለን ወደ ቤጌምድርን

እቴጌን ልንማርክ ልንመልስ ብድር። (*)

መጋረጃ።

፫ኛ ትርኢት።

(በእቴጌ መነን እልፍኝ)።

መነሱሴ።

ዛሬ ሌሊት በልሜ ያየሁት አስግቶኝ

ልነግርዎ መጣሁ ግርማዊት ያድምጡኝ።

ካሣና ወንድይራድ ሜዳ ላይ ተጋጥመው

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ወንድይራድ ድል ሆኖ ካሣ ሲማርከው

ሕዝቡም ተሰብስቦ አንተ ምራን ሲለው።

ካሣ በነጭ ፈረስ ወደርስዎ ሲመጣ

በርስዎ እየዛተ ሲፎክር ሲቃጣ።

ከቤተ መንግሥቱም ሲገባ ስላየሁ

ተደናገጥኩና ልነግርዎ መጣሁ።

*እቴጌ ግን በንግርቱ ካሣን ድል የምታደርግ ሴት ነች ስለ ተባለ ራስ ዐሊን ቀድመው ሄደው ጦርነት ገጠሙ።

እቴጌ (በቁጣ)

ሕልምም ቅዠት ነው ከፍርሃት የመጣ

ሌላ ሰው ቢነግረኝ በርግጥ እንዲቀጣ።

እርስዎም ዳግመኛ እንዲህ አይናገሩ

በሕልም በወሬ አይሸበር አገሩ።

ራስ ዐሊ (ከውጭ ይገባሉ)።

የሚያሳዝን ነገር መጣሁ ልነግራችሁ

ወንድይራድ ድል ሆኖ ተማረከላችሁ።

እቴጌ።

ይህን ዐይነት ወሬ ከወዴት ተሰማ

ከባላገር ነውን ወይስ ከከተማ።

ራስ ዐሊ።

እናቴ ይመኑ እርግጥ ነው ነገሩ

ወንድይራድ ተማርኳል አይጠራጠሩ።

ከጦርነቱ ላይ ሸሽቶ ያመለጠ

መጥቷል ሊነግርዎ ቀኛዝማች በለጠ።

መነሹሴው።

በሕልሜ ያየሁትን አሁን ስነግርዎ

አላምንም ብለውኝ ሐሰት ሲመስልዎ

ይኸውና ደረሰ ተረገጠልዎ።

ራስ ዐሊ (ለልፍኝ አሽከር)።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ሂድ ጥራው በለጠን

ነገሩን ዘርዝሮ በሥራት ይንገረን።

መነሹሴ

ቀኛዝማች በለጠ ሊያስረዳ ከመጣ

እስቲ ወጣ ብዬ ተመልሼ ልምጣ።

እቴጌ (በቀጣ)።

ይቆዩ ይቀመጡ!!

እርስዎም ነገሩን በሥራት ያድምጡ።

እቴጌ (ለበለጠ)።

አንድ ወንበዴ ሽፍታ መያዝ አቅቷችሁ

እርሱ ድል አድርጎ ትማረካላችሁ።!

ኧረ ለመሆኑ ምን ያክል ቢያይል ነው?

ድል ለመንሣትና ሊማርክ የቻለው።?

በለጠ።

ትላንት ላባቴ እንደነገርኳቸው (መነሹሴው ያፍራል)

ርግጥ ነው ነገሩ ድል የማድረጋቸው።

ዐሥር ፊታውራሪ ኻያ ቀኛዝማቾች

የተራ ወታደር ብዙም ባላባቶች።

አምስት ሺህ ሆነን ወደ ቁላው ስንወርድ

የሻለቃችንም የደጃዝማች ወንድይራድ።

ድል በማድረጋችወ ሆነው እርግጠኛ

ከነነፍሱ ያዙት ያንን ዐመፀኛ።

እያሉ በሰፈር ለሁሉም ሲመክሩ

በጣም እየዛቱ በጣም ሲፎክሩ።

መለከት ሲነፋ ሲመታ ነጋሪት

እርሱ ወደ እኛ ስንሄድበት።

የተከተለው ሰው እጅግ በማነሡ

ዐውቆ ሊማረክ እንው ይፈራል ለነፍሱ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

እያሉ ደጃዝማች በጣም ተደስተው

እነርሱም ወደኛ መጥተው ተጠግተው

ተማረኩ ብለን ብንልክበት ሰው

በነገሩ ስቆ አፊዞ መለሰው።

ወዲያው ግጥሚያ ሆኖ ገና ስንሚከር

ወንድይራድ ተያዘ ጥቂት ሳይከርከር

በፈረስ ላይ ሆኖ ሲመካ ሲወጠር።

ካሣ ተንደርድሮ በጦር ቢስተው

ጐራዴውን መዞ ተማረከ ቢለው

ከፈረሱ ወርዶ ቀኝ እጁን ሰጠው።

ራስ ዐሊ።

ተጠንቀቅ እያልኩት ስመከረው ወንድይራድ

በራሱ ሲመካ ደርሶ ሲመልስ ወንድ።

እቴጌ (በምሬት)።

ሆኖም ወንድይራድም ቢሸነፍ ቢዋረድ

ካሣ ሳይበረታ እኛ እንዝመትበት

ዐዋጅ ይመታና ሠራዊት ይከተት።

አሁን ባገኘው ድል ጎይል ሳይሰማው

ቶሎ እንሂድና እኛው እንግጠመው።

መነሹሴው።

ቅድሙንም ቢሆን ተናግሬ ነበር

ካሣ ንግርት አለው በዋዛም አይበገር።

በያድባራቱና በየባላገሩ

ወሬው ስለ ጸና ታውቆለት ንግሩ

አይጠረጠርም ተስፋ አለ በልቡ

ከቶ አይመለስም ሳይደርስ ከግቡ።

ይልቅ እንስማማ ጊዜ ከሰጠው

በከንቱ መጋፋት ከቶ ጥቅም የለው።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

እቴጌ።

በጣም ያሳዝናል የርስዎ ንግግር

ሽፍታ ይንገሥ የሚል ከየት አለ ንግር።

እንዲህ ያለውንም ከንቱውን ውዳሴ

እያነጋነናችሁ ደብተራ መነኩሴ (*)

እብሪት ላጠገበው ላመፀኛ ሽፍታ

ባነጋገራችሁ ሆናችሁ መከታ።

ፅሕፈት ሕልም ንግር አለኮ እያላችሁ

ዐመፀኛን ሁሉ ካበረታታችሁ።

ጥጋብ የሚገፋው እብሪትም የያዘው

ንግር አለኝ ብሎ ሊነግሥ ማለት ነው።

መካንንት።

ትዕቢተኛ ሁሉ በንግር ቢነሣ

አይቻልም ከቶ መሆን እንደ ካሣ።

ቅድሙን እናንተ በጣም ባታስቆጩት

መች ይሸፍት ነበር ይልስ እኔ ልሙት።?

ልቡን የታመነ ኩራት ያለበት ሰው

ምሕረት አያደርግም ንቆ ላኮሰውሰው።

ስለዚህም ካሣ በውነት አመረረ

መመለሻው ጠፋ ነገሩ ከረረ።

እኔ ልንገርዎ እውነተኛ ነገር

ካሳ ማሸነፉ ምንም ቢሆን አይቀር።

*በዚያን ዘመን ይልቁንም በጐንደር ቀሳውስትና መነኮሳት እጅግ ብዙ እንደ ነበሩና በንግርትና በትዕቢት ብዙ ፖለቲካ እንደ ሠሩ በታሪክ የታወቀ ነው።

ሕዝቡም ይኸንኑ በጣም ተረድቶታል

ትንሹም ትልቁም ባሳብ ደግፎታል።

እቴጌ (በቁራጥነት)

እንዲህ የምትሉ ፍርሃት ገብቷችሁ

ያሸነፈ እንደሆነ የት ልግባ ብላችሁ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

በጣም ያሳዝናል እንደዚህ መዋለል

ቀርጠኛው ሲመጣ ፈርቶ መወላወል።

አያስመሰግንም ከቶ አይደለም ዘዴ

እኔ ግን አልፈራም ቁርጧል አንዴ ሆዴ።

መስፍኖች እያሉ አይነግሥም ወንበዴ

ታማኝ አሽከሮቹን ይገፍ እኔ እዘምታለሁ

ለክብሬ ላልጋዬ እኔ እጋደላለሁ።

ራስ ዐሊ (በንዴት አነጋገር)።

ንግርትም ቢኖረው ሕልምም ቢታይለት

ኢትዮጵያ ለርሱ ከቶ አትገዛለት።

ለጊዜው ቢቀናው ቢመስል አሸናፊ

ማን ይገዛለታል ለዚህ ለተጋፊ።?

ከጐንደር ከጐጃም ከትግሬ ካማራ

ባላባት መሳፍንት በቶሎ ይጠራ።

ይህን አምባገነን ወንበዴና ሸፍታ

ሁላችን ተባብረን ባንድነት እንምታ።!!

መጋረጃ።

የእቴጌይቱ መማረክ።

በጦር ሰፈር ላይ ተማርከው ደጃች ካሣ ዘንድ ይቀርባሉ።

ካሣ (በማፌዝ አኳኋን)።

የጠሉት ይወርሳል የሚሉት ተረት

በርስዎ ደረሰ እቴጌ ይረዱት።

እርስዎም ያውቁታል መኖሩን ንግርት

በጣም አይዘኑ ግርማዊት ንግሥት

እንዲህ ይበቃል የሴት ነገሥታት።

በመስፍኖች ዘመን ምንም ሞያ አልታየ

ሕዝቡ በመሪ እጦር እንዲያው ተለያየ። (*)

መንግሥትን ለመምራት ያስቸግራል በጣም

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

እንደነራስ ዐሊ ሰው እምናቅ አይበቃም።

ኢትዮጵያ አንድ ሁና ጠረፍዋ እንዲከበር

ወንድ ያስፈልጋታል ልቡ የማይበገር።

እቴጌ (በምሬትና በኩራት)።

ይመስልህ ይሆናል አንተ ያሸነፍኸን

እዜር ቢጣላን ነው ጎጢአት አበርክተን።

ይሁን ከፈረደ ከመጣ ቅጣቱ

እንለምነዋለን ይደርሳል ምሕረቱ።

አንተ ግን ልምከርህ አትኩራ በከንቱ

ከቶ አትገዛም አንተ ሳለ መሳፍንቱ።

*ሰባ ዓመት ያኽል መስፍኖች ንጉሠ ነገሥቱን በቤተ መንግሥት አስቀምጠው በሥልጣኑ ይሠሩበት በነበረ ጊዜ አንድ አካል የነበረው ሰፊው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ተከፍሎና ተዳክሞ እንደ ነበረ ታሪክ ይነግረናል።

እንደ ገለባ እሳት ላንዳፍታ ቢያበራ

ስምህና ዘርህ ያልፋል ካንተ ጋራ።

መንግሥት አቋቁሞ አልጋንም መውረስ

እንዳይመስልህ አንተ መጋለብ ፈረስ።

ካያት ከቅድማያት ተያይዞ የመጣ

የንጉሥ ደም የሌለው አልጋው ላይ ቢወጣ።

ከርሱ ጋር ቀሪ ነነው ያቆመው መንግሥት።

አንተም ባጋጣሚ ብትሆን ንጉሥ

እምቢ ያለህን ሁሉ ደሙን ብታፈስ።

አንተ ከሞትክ ወዲያ ይሆናል ፈራሽ

ለቀማኸው አልጋ የለህም ወራሽ።!!

ካሣ።

በንግግርዎ ይሰማል ንዴት

በጣም ያሳዝናል መሆንዎ ሴት።

አነጋገር ሲያውቁ ሙግትም ሲችሉ

ሰውን ለማስቁጨት ተስፋውን ሲያስጥሉ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ላመጡት ክርክር ባለመለስልዎት

ይህ የሚናገሩት ቢሆን በንዴት

ነገር መሠረቱ አያጣም እውነት።

እኔም ድኻ ብሆን አለኝ ዘር ውልደት

ከነጋሚዎቹ ከነፋሲል ቤት። (*)

ወደ ፊት ይገኛል የትውልዴ ቍጥሩ።

ለኔ ዘር አይሥጉ እርስዎ አይቸገሩ።

*መሳፍንቱና ነጋሚዎች ደኛች፥ ካሣ የነጋሚነት ተወላጅነታቸንው እንዳልተቀበሉ አድርገው ቢናገሩም አፄ ቴዎድሮስ በእናታቸው የንጉሥ ትውልድ እንዳላቸው ተረጋግጧል።

በመስፍኖች ዘመን መንግሥቱ ተዳክሞ

ጠላት ከያለበት ባንድነት አድሞ።

ኢትዮጵያን ለመውረር ደፍሮ ሲሞክር

ሂድ አድናት ብሎ ላከኝ እግዚአብሔር።

ተባብረን ባንድነት እንድንከላከል

ፈቃዴኮ ነበር ከናንተ ባልበደል።

አላስብም ከቶ ለዘሬ ምኞት

በድሌ እንደወጣሁ በድል ይወጡት።

ያቀድኩትን አሳብ ወራሽ ሥራዬ ነው

ያቀድኩትን አሳብ የሚፈጽመው ሰው

ኢትዮጵያን አንድ አርጎ ጥበበን አስፋፍቶ

እኔም ከሞትኩ ወዲያ ምኞቴ አስማምቶ

የሚፈጽምልኝ ከመጣ ንጉሥ

አያሳዝነኝም የኔ ልጅ ባይነግሥ።

ላሁን ይበቃናል ተናግረናል ብዙ

እርስዎም በግዞት ሄደድው ይተክዙ።

(እቴጌ ይሄዳሉ)።

ካሣ (ለወታደሮች በኃይል አነጋገር)።

ታጠቁ ወታደር እንሂድ ተነሡ

በትግሬ በጐጃም እስኪሰማ አዲሱ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ራስ ዐሊ አድሞ ከትግሬ ከጐጃም

ሊወጋን አስቧል ተቆጭቶ በጣም።

መቶ ኻያ ሺ ሰው ሰብስቦ አሰልፏል

መይሳው ደፋር ነው በርግጥ ያሸንፋል።

እንሄዳለን እኛ በድላችን ተፈሪ

ኢትዮጵያ እስክትሆን ባንድ ሰው ተመሪ።

ወንድነቱን ዐውቆ ዕድሉን ሲያምነው

ዐላማውን አይቶ ከጸና ተስፋው

ማመንታት መሥጋትም አይገባውም ሰው።

ልባችን ጠንካራ ምኞታችን ሰፊ

ካሰብነው እንክንደርስ እንሁን ተጋፊ።

እኔን ተመልከቱኝ ፈረሴንም እዩት

ከግንባር ነው እንጂ ከኋላ አታገኙት።

ተከተሉኝ ጐበዝ እኔ ነኝ መሪያችሁ

ድል በዕድል እንዳለች አሁን ላሳያችሁ።

እንግዲህ ቁራርጠው በፈንዜ በካራ

እጅህ እንዳይሣሣ ወታደር አትራራ

ነፍጥና ጐራዴ እንደ ልቡ ይሥራ።

(ወታደሩ ይፏከራል)።

መጋረጃ።

፩ኛ ትርኢት።

በጦር ሜዳ ላይ አፄ ቴዎድሮስ ከነመኳንንቶቻቸው።

የጐርጐራ ጦርነት።

አዝማሪ።

ጐርጐራ ጐርጐራ ጐርጐራ ጐርጐራ

ገነት እምሳይ አገር ስምሽ የተጠራ

በላይሽ ያበራል የፀሓዩ ጮራ

ጣና መስተዋት ነው ላንቺ የሚያበራ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ልምላሜ ሰጥቶሻል ውበት የሚያኮራ

ያየሽ ሁሉ አድንቆ ለሰሚ እንዲወራ።

ባንቺ በመልካሚ በለምለሚ ሜዳ

ድል በዕድል ተገኝታ አንዱን ስትከዳ።

ወንድነቱን ዐውቆ ቁርጦ የተነሣ

ራሱን ተማምኖ አሸንፈ ካሣ።

አንድ ለሺ ሆኖ ሲጋፈጥ አልፈራ

የቁረጠ ልቡ ታየ በጦራጦር።

ባላባት መሳፍንት ከሰሜን ከጐጃም

ከትግሬ ከላስታ አብሮ ቢመጣም

ዐውቆታል ዕድሉን መይሳው አልሠጋም።

ዐላማውን ዐውቆ ቁርጦ ልቡናው

ሰብሮ ሰብሮ ጣለው እያገሳ አንበሳው።

የጦርጦራ ሜዳ ጠበበው ፈረሱ

መላ ኢትዮጵያን ይርገጠው ራሱ።

ከመቅደላ እስኪደርስ አይቁምም ትንፋሹ።

ገብርዬ።

ራስ ዐሊ ከሸሹ ከሞቱ እነጐሹ

እንዲህ ማናለ ከኛ ጠብ የሚሹ።?

ገልሞ።

ማንም አያግደን ድል ያንተ ነችና

ስምህን ንገረን እናንግሥህ እኛ።

ካሣ።

ሰሜን ሰሜን እነግሯችኋለሁ

ደረስጌ ማርያም ዘውዴን እጭናለሁ።

ውቤ ከጦርጦራር በሸሸት አምልጧል

መቼም ጎይላችንን ገምቶት ዐውቆታል።

አልገዛም ካለ እንዘምትበታለን

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ዝም ብለን አንቂይ ባላንጣ እያለን።

ውቤን ድል ስናደርግ ሽዋ እንዘምታለን

ኃይለ መለኮትን እናስገብራለን።

፮ኛ ትርኢት።

(የደጃች ውቤ መማረክ)።

ደጃች ካሣ።

ዘውዱን አዘጋህቲ አቡን አስመጥቶ

መንገሥ ያልደፈረ በዕድሉ አመንትቶ።

ሊያዝን አይገባውም ባለ ዕድል ቢቀማው

ለደፋር ብቻ ነው ዕድል የተሰጠው።

ዕድሉን ተማምኖ በዕድሉ የገፋ

አሸናፊ ሆነ ድል አርጎ በተስፋ።

እግዚአብሔር መርቆ ዕድል ለሰጠው

አልገዛም ብሎ እሚቃወም ሰው።

በከንቱ ይለፋል ድሉን ላያድግ

መገዛቱ ላይቀር በውድም በግድ።

ደጃች ውቤ።

ዕድልን ተማምነው ድልንም ቢያገኙ

ተሰጥቶኛል ብለው መግዛትን ቢመኙ

እግዜር ካልፈቀደ አይረጋም መንግሥቱ።

ነጋሢ ባላባት አይቀር መነሣቱ

ልከራከር ብሎ ለገዛ መብቱ።

ዕድሉን ያወቀ ራሱን ያመነ

በራሱ ተነሥቶ በኃይል የገነነ።

ጊዜ እሰጠው ድረስ ቢሆን አሸናፊ

ጠላት ይበዛዋል በኃይሉ ተጋፊ።

እርስዎም እንደዚህ ቢመኩ በዕድልዎ

በፍርሃት በሥጋት ተገዛሁ ቢልዎ

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

አይቀርም መክዳቱ ቀንስ ሲጐድልብዎ።

ኃይልና ጭካኔ ብርታትና ጀብዱ

አይበቁም ለመግዛት በዘዴ ካልሄዱ።

ዳኝነት ጠብቆ በሚዛን የሄደ

ተወዶ ተከብሮ ብዙ ተራመደ።

ካሣ።

ጥንቱን ከጧቱ እግዚአብሔር ቀባኝ

ኢትዮጵያን ግዛ ብሎ ፈጠረኝ

ድፍረት ኃይል ብርታት ተስፋንም ሰጠኝ።

ጠላቶቹ ሁሉ አይቆሙም ከፊቱ

አንዴ ቀብቶኛል አይቀርም መግዛቴ።

መጋረጃ

፯ኛ ትርኢት።

የአጼ ቴዎድሮስ መንገሥ።

ደጃች ካሣ ዘውድ ጭነው ዳግማዊ ቴዎድሮስ ተብለው ሕዝቡ ሕዝቡ እልል ሲል ዘውድ በራሳቸው ላይ አድርገዋል ላይ አድርገዋል ጃንጥላ አሲዘዋል እነገብርዬና ዋና ዋናዎቹ አርበኞቻችወ አቡነ ሰላማም አብረው ቁመዋል ነጋሪት ይመታል መለከት እምቢልታም ይነፋል። ፊታውራሪ ገብርዬ የአፄ ቴዎድሮስን ዐዋጅ ያነባል።

ፊታ/ገብርዬ።

ወታደር መኳንንት ካህናት ባላገር

ነጋዴ ገብሬ የኢትዮጵያ አገር።\

ትግሬ ጐጃም ሸዋ ወሎና በጌምድር

ዐፄ ቴዎድሮስ ነግሷል በፈቃደ እግዚአብሔር

ከዛሬ ዠምሮ ቴዎድሮስ ነው ገዥዎ

አገር አንድ አድርጎ ፍርድን የሚሰጥ።

ፈላሻና ቅማንት ክርስቲያንና እስላም

ተስማምተህ ተባብረህ እንድትኖር በሰላም።

በዘር በሃይማኖት ቀርቷል መለያየት

ሁሉም እኩል ይሁን በኢትዮጵያዊነት።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ተለያይቶ መኖር ምንም ጥቅም ይለው
አቅም እያነሰ ኋላም መውደቅ ነው።
በዙሪያ የሚያስተውሉ ምቀኞችን ብዙ
ጉልበት አሳጥተው ለያይተው ሊገዙ።
ተባብረን እንሥራ አይግባን ስንፈት
ኢትዮጵያ እንድታገኝ ክብርና ልማት
ጥበብ ሥልጣኔ ሀብት እንዲሆናት።
ሰላም ሥልጣኔ እንዲታይ ለምልሞ
በዘመነ መስፍን መንግሥቱ ተዳክሞ።
ጥንታዊት ኢትዮጵያ አንድነቷ ጠፍቶ
የቀድሞ ጠላቷ በያለበት መጥቶ።
ያስባል እስካሁን ገባር ሊያደርጋት
ሃይማኖት አስክዶ ክብር ሊያሳጣት።
ምን እንኳን አደጋው የሚያሠጋ ቢሆን
ማንም አይደፍረንም ልበ ሙሉ ከሆን።
ጠላት አያስብም ገባር ሊያደርገን
በርጥ እንችላለን መኖር ተከብረን።
አሳቤ ብዙ ነው ታዛኝ ከሆናችሁ
እውነተኛውን ጥቅም ካመዛዘናችሁ።
ላገር ለትውልዱ ካሰባቹ በእውነት
ምቀኝነት ተንኰል ከተዋችሁ ስንፈት።
እንደ ቀድሞ አባቶች ጀግኖች ከሆናችሁ
ሰላም ጸጋና ክብር ጥበበ ላስገኛችሁ።
እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ መሪ ያደረገኝ
ይህን ዘውድ ሰጥቶ አደራህን ያለኝ
ልቤን መርምሮ ነው በጣሙ ቢያውቀኝ።
እኔም አደራዬን እጠብቃለሁ
ለኢትዮጵያ አንድነት ከልብ እሠራለሁ

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ስሟን አስከብሬ እሞታላታለሁ።።

ይህን አደራዬን ለመፈጸም ስጥር

ካላገኘሁ ከሕዝብ እርዳታና ምክር

ቅንነት በማጉደል እንቅፋት ቢፈጠር

እኔ ነኝ ጠላቱ በጣም የምጨክን

የደም እንባ ቢያለቅስ ጥቂት የማላዝን።።

አድምጠኝ አድምጠኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ

ተቁጭኽ እኔ ነኝ አሳቢህም ከልብ።።

ወደ ፊት እያደግህ እንድትራመድ

እኔ አሳይሃለሁ የጀግና መንገድ

ተከተለኝ በውድ ባትወድም በግድ።።!!

አቡነ ሰላማ።።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

ዳግማዊ ቴዎድሮስ ይኸውና ንጉሥ

ሃይማኖት ጠብቆ ጠላት ይደምስስ።።

ሁላችሁ አደራ ባንድ ሃይማኖት ጽኑ

ቴዎድሮስ ምኞቱ ነው ልባዊ እንድትሆኑ

ኢትዮጵያ አንድ ሆና እንትሠለጥኑ።።

አጼ ቴዎድሮስ

(ለወታደሮቻቸው)።።

ጠላትን ማሸነፍ መንገሥም አይበቃም

ትግላችን ገና ነው አለን ብዙ ድካም

ሕግ ደንብ አውጥቶ ሰላምን ማቋቋም

ከፍ ያለ ሥራ ነው አስቸጋሪ በጣም።።

እስካሁን ከኔ ጋር ብዙ ደክማችሁ

እንዲሁም ወደ ፊት እርዱኝ ከልባችሁ

አገር እስኪቀና አይተኛ አሳባችሁ።።

ጥቂጥ አርፈፍ በለን ደግሞ እንነሣለን

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

በወሎ በሸዋ እንገሠግሣለን።

እዚያም ያለው ንጉሥ ኃይለ መለኮት

ጎይል ብርታት አለው ጽኑ ሃይማኖት።

ሕዝቡም ጠንካራ ነው ጌታውን ደጋፊ

አይደለም ደካማ ዋላ ተሸናፊ።

ጐጃም ትግሬን ሸዋን ካረግነው ጥገኛ

ሥጋት የለብንም የሚያስፈራ ለኛ።

ዓለሜ።

ከቋራ ገሥግረን አብረን ስንዋጋ

ጌታችን ሲነግሡ እኛ አገኘን ዋጋ።

አሁንም ካንተው ጋር በድል እንገፋለን

ትእዛዝህን ልንፈጽም እድር መሀላ አለን።

እንኳንስ ድል በድል ክብር ለማይለው

አንድ ቀን ላበላው ይሞትለታል ሰው

መጋረጃ።

ክፍል አራተኛ።

፩ኛ ትርኢት።

በተጐለት አታክልት በሚባለው ቦታ በንጉሥ ኃይለ መለኮት ቤተ መንግሥት ንጉሡ ታመው በአልጋ ላይ ናቸው።

የእልፍኝ አሽከር።

የሸዋ ባላባት መኳንንቱ ሁሉ መጡ ከያገሩ

ከግርማዊ ንጉሥ እንዲመካከሩ።

ንጉሥ ኃይለ መለኮት።

በል ይግቡ ጥራቸው

እንዲከላከሉ ትእዛዝ እንስጣቸው።

(መኳንንቶቹ በተራ እየገቡ እጅ ይነሣሉ)።

እንዴት ሰነበትክ ሰይፉ ዳርጌ፥ አንዳርጋቸው ሀብተ ማርያም፥ በዛብህ ሀብቱ፥ ገርማሜ፥ ን አደው አዝብጤ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ኃይለ መለኮት (ለጸሓፊያቸው)።

ጻፍላት ለወርቂት ብትሰማ ምክር

ቴዎድሮስ የሚባል ሰው ነግሦ በበጌምድር

ታጥቆ መጥቷል አሉ እኛን ሊያስገብር።

ሰውዬው ብርቱ ነው ብዙ ጎይል ያለው።

እኔ ከግንባር ነኝ አንቺ ከኋላው

እንበለው ባንድነት እንድናደከምው።

ብትሰሚ መልካም ብትቀበይ ምክሬን

እኔ ቁርጫለሁ ላላስነካ አገሬን።

ይህንን ደብዳቤ ፈረሰኛ ይዞላት

ለወይዘሮ ወርቂት ቶሎ ያድርስላት።

ንጉሥ ኃይለ መለኮት።

አሳብ ሥጋታችን ከቶ አይደለም ስውር

እኛንም ሊያስገብር መጣ ከበጌምድር።

ቴዎድሮስ ነኝ እያለ ለኢትዮጵያ መሪ\

በጐንደር በጐጃም በትግሬ አሸባሪ።\

(ንጉሥ ኃይለ መለኮት ባልጋ ላይ እንዳሉ ከሸዋ መኳንንቶች ጋራ ይመካከራሉ)።

ዘውዱንም ቀምቷል ዐፄ በጕልበቱ

ይረጋ ይመስል በርሱ እጅ መንግሥቱ።

ጊዜና ሰውዬ በዕድል ተገናኝተው

አስጊ ሆኗል ለኛም ገኗል የቋራው ሰው።

እኔ እንኳ ብታመም በእግዜር እጅ ብያዝ

በርቱና ተዋጉ ተጉለት ይፋት መንዝ።

ዘውዱን በሸፍትነት ለቀማ በግድ

መገዛት አይገባም ክብርን ማስወሰድ።

የግሀለ ሥላሴ እንዳይነካ አልጋው

ለልጆቹ አቁዩት ገና ገዥ ነው።

አሁን ቢያስፈራችሁ የመጣው ከወዲያ

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

በከንቱ ያስባል ሊነግሥ በኢትዮጵያ።

ሕዝቡን በሴፍ በሳት የሚያሠቃየው

ከሰሎሞን ትውልድ ዘር ስለ ሌለው

በከንቱ ይለፋል ላይሆን ያሰበው።

ያቀዳቸውንም የሚፈጽሟቸው

የሣህለ ሥላሴ የኔ ልጆች ናቸው።

አገር አንድ እንዲሆን ቴዎድሮስ በማሰቡ

ያመሰግነዋል ከፍ ያለ ነው ግቡ።

አገርም አንድ ሆኖ ሕዝብ ወዶ እንዲገዛ

ዘዴ ትዕግሥት ያሻል ከቶ አይደለም ዋዛ።

ስለዚህም ቴዎድሮስ በታም ተሳስቷል።

ኃይልና ጭካኔን ተማምኖ ተነሥቷል።

ዘዴ ካልጨመረ ካልለወጠ እርምጃ

በውጥን ይቀራል መቁየቱን እንጃ።

ሆኖም ባካሄዱ ቢሣሣት በጣም

ሐሳቡን ለማቅለል አይቻለንም።

ልጄን ምኒልክን አደራ ልስጣችሁ

እሱ ነው ወራሼ ወደ ፊት ገዥያችሁ።

አገርን አስማምቶ የሚያኖር በሰላም

የኢትዮጵያንም ስም የሚያሳውቅ ላለም።

ለሣህለ ሥላሴ እንዲሆን ዕድል

አለው ልጅ ወደ ፊት የሚጠቀልል።

ሕግ አውጥቶ ገዥ በደንብ አሳዳሪ

ጥበብ ሥልጣኔ ለሕዝቡ አስተማሪ

ብዙ መሃያ ያለው በስሙም ተፈሪ።

ስማኝ ያገሬ ሰው ይንቃ መንፈስህ

ዕውቀትና ብርታት እግዚአብሔር ይስጥህ።

ተስማምቶ ለመኖር እንዳይሳንህ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ይወጣሉ ጅግኖች ከገደሎችህ።

ከሕዝብ ካባላባት ደግሞም ከመስፍኑ

ከነርሱም ተወልደው የሚመሰገኑ።

የተባለው ሲሆን ንግርቱ ሲደርስ

ብርሃንና ሰላም ጥበብ ሲለግስ።

ባፍሪካ በእሲያ ባውሮፓም ጭምር

ትወደድ ኢትዮጵያ በጣም ትከበር።

አቶ ሀብተ ማርያም።

ጌታችን ያሉትን ሰምተነዋል ምክሩን

ማነው የማይረዳ ሲቻለው አገሩን።

ለንጉሡ የማይሞት ለክብር የማይጋደል

ሊኖር አይገባም ከወንዶች መካከል።

አቶ ዳርጌ።

ወንድሜ ንጉሡ እንደ ተናገሩት

ለክብር ላልጋችን ተግተን እንሙት።

ቴዎድሮስ ቢመጡብን ጎይላቸውን ታምነው

ሸዋን አይገዙትም ራሱ ገዥ ነው።

አቶ ሀብቱ።

እግዜር ካመጣብን የማንችለውን

አንገብርም ብለን ከተከራከርን።

ምን ያስፈልገናል ከእግዚአብሔር መጋፋት

አቅምን መዝኖ ነው ጠላንትም መጉዳት።

አቶ አዝብጤ።

አያ ሀብቱ አብለው እኔም እስማማለሁ

ጊዜው ካልፈቀደ አይባልም እኔ አለሁ።

ጊዜ የሰጠውን መልሶ እስኪክደው

ዘዴ መፈለግ ነው እንዲበርድ ቁጣው።

አቶ አንዳርጋቸው።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

እኔ አልቀበልም እንዲህ ያለ ዘዴ።

መከላከል ሲቻል በጦር በጦራዴ

ባገሬ በሽዋ አይነግሥም ወንበዴ

ተዋግቶ ለመሞት ቁርጧል አንዴ ሆዴ።

አቶ ግርማሜ።

ጎይልና ጭካኔ ሰውን አይገዛውም

ፍቅርና ምሕረት ይበልጣል ከሁሉም።

ትዕግሥት ደግነት ምሕረትም ያወቀ

እውነትን ፍርድንም ከልብ የጠበቀ

በፍቅሩ እየገዛ በኂላም ጸደቀ።

እግዚአብሔር መርቆ የቀባውን ገፍቶ

እነግሣለሁ የሚል ጥጋበኛ መጥቶ

ተገዙ ገብሩ ቢለን አንሰማውም

ይህንን ግፈኛ ሸዋ አይቀበለውም።

አቶ ሰይፉ።

አንተም ብትታመም ጤና ቢነሳህ

ልጅ ወልድሃልና ማንም አይወርስህ።

ከሣህለ ሥላሴ ያለን በረከት

ለመላው ኢትዮጵያ ይሆነዋል ሀብት።

መንዝ ተጉለት ይፋት ቡልጋና ሸንኮራ

መረሐቤቴ ዶባ ይፍራታና ጠራ

ግድም ወግዳ ጅሩ ሞረትና ደራ

ይዋጋል ጠንክሮ በነፍጥ በካራ።

ላባታችን አልጋ ላገራችን ክብር

ሕይወታችን ያልፋል ስንከራከር።

አቶ በዛብህ።

እስከ ዛሬ ድረስ ማንም አልደፈረን

እንዴት ለተጋፊ እንገብራለን።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ለምንወደው ጌታ ላገራችን ንጉሥ

ግዘት መሐላ አለን ደማችን እንዲፈስ።

በገደል በጫካው እንመክታለን

ለጌታችን አልጋ እንጋደላለን።

ላረግነው መሐላ ለሰጠነው ቃል

እምነትን ጠብቆ መሞት ይገባል።

አቶ ናደው።

ቀርጠኛው ከመጣ የማይቀረው ግድ

መጋፈጥ አለብን ክብር እንዳይወስድ።

በየተረተሩ በገደል በጫካ

ይገባል መመከት አልጋው እንዳይነካ።

እንዴት እኛ እያለን ታማኝ አሽከሮችህ

ደማችን ሳትፈስ ይማረካል ልጅህ።

ንጉሥ ኃይለ መለኮት።

የትግሬ የጐጃም፥ የወሎ ሕዝብ ሁሉ

ካሣ አይነግሥም ብለው ይከራከራሉ።

ጎብረት ሙያና ልብ ካላጓደላችሁ

ቀድሞ አባቶቻችን ክብርን ያቁዩልን

ላገር ለሃይማኖት ስለተሠውልን

መሆኑን በማሰብ ልባችሁ ከፍ ይበል።

መክቱ ባንድነት ትውልድ እንዳይበደል።

መጋረጃ።

(በመጋለረጃ ውስጥ) አዝማሪ በገለሌ።

ገለል ገለሌ ገለል ገለሌ

ቂራጥ ወንድ ልጅ አይወላውሌ።

ዝም ትላለህ ወይ አገር ሲወረር

ታጠቅ ተነሣ የንጉሥ ወታደር።

ደፋሩ መጥቷል ቂርጦ በሞቱ

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

አምጣ ወልዳ የጀግና እናቱ።።

ደሙ መራር ነው ኮስታራ አሞቱ።።

የማንን አገር ማን ይወርሳታል

የማንን እርስት ማን ይመራታል

የማንን እናት ያዋርዳታል

ወንድ ልጅ አላት ያስከብራታል።።

ባፋፍ በገደል እስቲ ተጣሩ

ሸዋን ሊወረው መጥቷል ደፋሩ።።

መራር ቁለኛ ሞትን አይፈሬ

ቁራጥ ደግኛ እምቢ ላገሬ

እይወላውልም አይስም ጦሬ።።

ተው ሂድ ፊት ለፊት ግምባር ለግምባር

አንዴ ከመጣ ሞት እንደሁ አይቀር

አያምርበትም ወንድ ልጅ ማፈር

ጠላት ሲመጣ አንገት ማቀርቀር።።

ካፋፍ ማዶ ከሜዳው ላይ

ፈረስ ሲያስካካ አትሰማም ወይ።።

አይጠረጠርም እነሱ ናቸው

ሽንጥህን ገትር ቁመ በላቸው

ግምባር ለግምባር ሂድ ግጠማቸው።።

(በሰንሳ) ምት።።

ፈሪ ሲደበቅ ከሞት አምልጦ

ደፋር ሲመጣ ዐይኑን አፍጦ

የሞተው ጀግና ልቡን አጋፍጦ።።

ጉበዝ ሲመክት ውርድትን ጠልቶ

ይነሣል እንጂ አይቀርም መውቶ።።

(በገለሌ)።።

ለጌታው ታማኝ የማይወላውል

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

የቁርጡ ለታ ይገኛል በውል።

መጡብህ ሲሉት በፈረስ በግር

ተው በለው አለ ፈረስክን አዙር።

ጠላት አይወድም ገርርባ ሲያሳዩት

ግምባር ለግምባር ዐይን ዐይኑን በሉት።

አካኪ ዘራፍ ሞትን አይፈሬ

አመታት ያውቃል የጦር ገበሬ።

እምቢ አሻፈረኝ ሞት ይሻለኛክ

ያለንጡሜ ማን ይገዛኛል።

በሰንጐ።

አሸከሩ ሲወድቅ ጌታው ሲጋፈጥ

ይገድላል እንጂ መች ይምራል ነፍጥ።

ማን ይደፍራታል ያገሬን ልጅ

ማን ይረግጣታል የቤቴን ደጅ

ደምና ሬሳ ይሆናል እንጂ።

(በሽለላ)።

ተው ተው አትጨነቅ አታመንታ ጐበዝ

አይቁርጥም ጐራዴ ገና ሳይመዘዝ።

ተው ተው ተው ተው እያየህ ተራመድ

እሳት ሳይቃጥል መች ይሆናል አመድ።

ገብሩ ተገዙ ይለናል ደፋሩ

አውራው ካልተያዘ መች ይቀዳል ማሩ።

በለው በለው አሳየው እንግዲህ

ወትሮም ቁርጦ እምጣል የቁየ ልማድህን።

(ጥቂት ጊዜ ቁይቶ) ስለ ንጉሥ ኃይለ መለኮት አልቃሽ (በዜማ)።

አገሩን ለማዳን ሲያስብ በውነት

እንደ ኮራ ሞተ ኃይለ መለኮት።

ርስት መች አነሰው በመንዝ በተጉለት

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ራሳውን ወስደው የሚያንገላቱት።

ዐፄ አላምንም ብለው ሞቷል ቢሏቸው

ራሳውን አውጠተው አዩት ባይናቸው።

እንዴት ቢፈሩት ነው እንደ ክርስቶስ

ሞቱን ያላመኑት ዐፄ ቴዎድሮስ።

የሸዋና የጐንደር፥ መኳንንቶች አቤቶ ምኒልክ አፄ ቴዎድሮስ በንጉሥ ኃይለ መለኮት ቤተ መንግሥት አቶ ዳርጌ አቶ ገርማሜ አቶ አብቱ አቶ አንዳርጋቸው።

አፄ ቴዎድሮስ።

ከቶ ለምን ይሆን ምኒልክ ያለው?

ምን ይሆን ላባቱ በስሙ የታየው።?

አቶ ዳርጌ።

የምኒልክን ስም ጠርተው የሰጡት

ዘሩን ሲጠቅሱ ነው ከሰሎሞን ቤት

ከጥንት የመጣውን ከሳባ ንግሥት

ልጇ ይወርሳል ሲሉ ያባቱን መንግሥት።

አፄ ቴዎድሮስ (በማፌዝ)።

ሞያ ሳያሳዩ በስም መመካት

አጭር አስተያየት ከፍ ያለ ስሕተት።

ዐዋቂ ሲመስለኝ ኃይለ መለኮት

እንዴት ብሎ አመነ በስም በትንቢት።

ይሁን ምን ቸገረ በስም ከደረሰ

ምኒልክ በስሙ አልጋ ከወረሰ

አባቱም የሰጠው ስሙ ይቂይለት

መንግሥቱን ለመውረስ ተስፋ ከሆነለት።

(ለአቤቶ ምኒልክ)።

ለመሆኑ አባትህ ሌላ ምን ሰጥቶሃል?

በአንገትህስ ላይ ምን ነገር አስረሃል።?

አቤቶ ምኒልክ።

አባቴ ሳይሞቱ አንድ ቀን ተጣርተው

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ብቻዬን ከጓዳ እጀንን ይዘው ገብተው

ይህን አሠሩልኝ እንዳይጠፋ ብለው።

አፄ ቴዎድሮስ

ኧረ እስቲ እኔ ልየው ይገባል መጠርጠር

ውስጡም ታላቅ ምጢር ሳይኖርበት አይቀር።

ካንገቱ ላይ በሰንጢ በጥሰው ቆዳውን ቀደው ጽሕፈቱን ያወጡና ያነባሉ።

«አንተ ነህ ምኒልክ የኔ አልጋ ወራሽ

ብር ወርቅ መሣሪያ የሚቁጠር በሺ

ከትልቁ ዋሻ ይገኛል ብትሽ»።

(ለመካንንቶቹ)።

አያችሁ አያችሁ የሸዋ ብልጠቱ

ክታብ አስመስሎ ያሰረው ባንገቱ

ወርቁንና ብሩን ሲደብቅ አባቱ።

(ለገብርዬ)።

ገብርዬ መሪ ይዘህ ከዋሻው ገብተህ

በቶሎ እንድትመታ ያለውን አስጭነህ።

(ለአቤቶ ምኒልክ)።

አንተ ገና ልጅ ነህ እኔ ልውሰድህ

ብልህ ትመስላለህ ባስተያየትህ

ብዙ ታጠናለህ ከኔ ጋራ ከሆንህ

አገሩም ይጠበቅ ባንዱ ባጐትህ

ለወግ እስክትበቃ እኔ እስክሾምህ።

መጋረጃ።

አምስተኛ ክፍል።

፩ኛ ትርኢት።

አፄ ቴዎድሮስ በጐንደር ቤተ መንግሥት በዙፋን ተቀምጠው እቴጌ ተዋበች በጐናችው ቁጭ ብለዋል።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

አፄ ቴዎድሮስ።

ጐጃም ትግሬ ወሎ ሸዋም ከገበረ

እንግዲህ ምናለ መንግሥቴ ከበረ።

አገሩን በሰላም የማስተዳደሩን

እንገሥምር እንግዲህ ደንብ ማቋቋሙን።

መቅጠር ያስፈልጋል አያሌ ወታደር።

ሕዝብ ተጨቁኖ በገሃር እንዳይበደል

ገባር ሥራት ቀርቶ ደመውዝ እንዲቀበል።

ባሪያም መሸጥ ይቅር በበርቱ ይከልከል።

ቀሳውስቱ በዝቶ ወታደር እንዳያንስ

በየደብሩ ያለው ካህኑ ይቀነስ።

ጋብቻ እንዲጸና ይቅር መፋታት

ክርስቲያን ይጋባ በሕገር ሥርዐት።

አውራጃ ቀበሌው በመንግሥት ይገዛ። (*)

በእስላም በክርስቲያን ያለው ልዩነት

እንዳይቀንስብን የሕዝቡን ጎበረት

በተቻለ ዘዴ እንፈልግለት።

ሥልጣኔ እንዲገኝ ይስፋፋ ትምህርት

ሕዝቡን ማስተማር ነው ብረትን መሥራት።

*ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ውሳኔዎች አፄ ቴዎድሮስ በዐዋጅ አጽንተዋቸው እንደ ነበረ ታሪክ ያረጋግጣል።

ለወጣቱም ሆነ ለሽማግሌው

ካባት የወረሰው ሌላ ለሌለው።

አስፈላጊ ይሆናል ማሳየት ብርታት

በልቡ እንዲጸና የዘሩ ኩራት

ኢትዮጵያ አንድ ሁና ስትተባበር

ጎይሏን አጠንክራ ራስዋን ታስከብር።

እውቀት ባገር ሰፍቶ ሲኖር በሰላም

እሄዳለሁ እኔ ኢየሩሳሌም።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

የጌታን መቃብር በክብር ላቆም

ምእመናን ሁሉ ሄዶ እንዲሳለም።

ንሴብሖ እያለ ለመድኀኔ ዓለም።

መጋረጃ።

፪ኛ ትርኢት።

አፄ ቴዎድሮስ በዙፋናቸው ተቀምጠዋል።

ገብርዬ (ከውጭ ይገባል)።

ጌታዬ ሰማሁኝ የሚያሳዝን ወሬ

ሸፍቷል ይላሉ ሸዋም ሆነ ትግሬ

ዓለሜ (ከውጭ ይገባል)።

ባማራ ልጅ ጋረድ ደግሞም ብሩ ኃይሉ

እንዲሁም በጐጃም ደጃች ተድላ ጓሉ

ዐፄን ለመቃወም ተነሥተዋል አሉ።!

ገልሞ (ከውጭ ይገባል)።

በላስታና በዋግ ታቹን በተከዜ

አገር ሳብሯል ያ ዋግዙም ጐበዜ።

እንዲሁም በተንቤን ደጃች በዝብዝ ካሣ

አልገዛም ብሎ ሸፍቶ ተነሣ።

በትግሬ በሺሬ ወልቃይትን ይዞ

ሸፍቷል ጐበዜ የተባእልው ጥርሶ።!

አፄ ቴዎድሮስ (በምሬትና በቁጣ)።

እኔም የፈራሁት ይህንኑ ነበር

ምቀኛ በቶብኝ በውጥን እንዳልቀር (ብድግ ይላሉ)

ደንቁሮ! ምቀኛ! ተንኮለኛ! ከንቱ!!

እንግዲህ ምንድነው ለዚህ መድኀኔቱ?!።

ተገዙ ባላቸው አንገዛም ካሉ

በሳት ተለብጠው በሰይፍ ይቀጣሉ።

መጨከን ነው በጣም እምቢ ለሚለው

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ዐውቆ ነው በጣም እምቢ ለሚለው

ዐውቆ ለሚያጠፋ መካርም የለው።

በጦር በጉራዴ ይመታል አገሩ

በኛ ፈቃድ ብቻ ታዘው እስኪመሩ።

ጎዘን ርኅራኄ እንዳታሳዩዋቸው

መልሶ ይከዳል መልቲ ነው ልባቸው።

ትእዛዜን አፍርሰው ዐመፅ ለሚያሳዩ

ጥቂትም አልሳሳ እኔ አልተውም መዩ።

አውራጆቹ ሁሉ በኔ አምደማቸው

ገብቶኛል ነገር ያለው በልባቸው።

ባላባት መሳፍንት እኛ አለን እያሉ

እኔን ለማስወገድ ሁሉም ያስባሉ።

እንደዚህ ከሆነ ሕዝቡም ያሚያስበው

በሴፍ በጉራዴ በሳት ነው የምለው።

እንድገዛ መርጦ እግዜር ነው የላከኝ

ግፍ ሠራህ እያለ ማነው የሚወቅሰኝ

የፈቀደው ቢሆን እጁ ከቶ አይሳሳም

የኔ ነፍሴ ቆማ ሌላ ሰው አይገዛም።

አሳቤን ሳልፈጽም ምን ቢሆን አልተኛም።

በጎይል እንደ ነገሥኩ በጎይል እገዛለሁ

ማንንም አልፈራም አንዴ ነግሻለሁ።

እግዜር ምን አቆጣው አንዴ ከሰጠኝ

እኔው እገዛለሁ እንደመሰለኝ።

(በትካዜ)።

የሚያራራኝ ማነው ሙታለች ተዋበች

ልቤን ያለመካር አስቀርታዋለች።

እሷን ሲወስድብኝ ሲለየኝ ከሚስቱ

በጣም ተሰምቶኛል ከእዜር መጣላቱ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

(በቁጣ)።

እንግዲህ እንዳሻው የፈቀደው ይሁን

መይሳው ደፋር ነው ያደርጋል የልቡን።!!

(ጦራዬውን ይመዛል)።

እምቢ ያሉትን ሁሉ እንዳትምሯቸው

በጦር በጦራዬ በሳት አቃጥሏቸው።!!

(ገብርዬ ገልሞና ዓለሜ ሦስቱም ባንድነት ጦራዬያቸውን መዘው)

እዘዝ! ዝግጁ ነን!

አገር አንድ እስኪሆን እንጋደላለን።!!

መጋረጃ።

፫ ትርኢት።

ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ቤልና አፄ ቴዎድሮስ ወደ ዘመቻ ይሄዳሉ ወታደሮቻቸው ተከትለዋቸዋል።

አፄ ቴዎድሮስ።

(ላንድ ባላገር)።

አንች ባላገር ወዬት አለች ጋረድ?

እናገኛት ይሆን በዚህ በኩል ብንሄድ።?

ባላገር።

ተረተሩን አልፈው ከወንዙ ሲደርሱ

ወንድሙንማ ቢሆን ወይም እርሱ ራሱ።

ሳያገኙት አይቀርም ከጥሻው መካከል

አድፍጦ ከጫካው ሊቃማና ሊገል።

ቤል።

ይህ ዐመፀኛ ሰው የቁረጠ ይመስላል

እያየን በማስላት ብንሄድ ይሻላል።

አፄ ቴዎድሮስ።

አዬ ጉድ ደግሞ አንተ ለርሷ እንዳትሠጋ

ማነው የሚሰጣት ይኸን ያክል ዋጋ

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ይመስልሃል እንዴ ደፍራ እኛን ልትወጋል?።

ቤል።

ሆኖም እንጠንቀቅ ከጫካው ስንደርስ

መንገዱ መጥፎ ነው አያስኬድም ፈረስ።

ዝግ ብለን እያየን አድምጠን እንሂድ

ለሽፍታ ይመቻል እንዲህ ያለው መንገድ።

ክፍል አምስተኛ።

ቤል ንግግሩን ሳይጨርስ በጫካው ሲያንኮሻኩሽ ይሰማሉ። ወዲያው ጋረድ ፎክሮ ጦር ይወረውራል። አፄ ቴዎድሮስ ጐንበስ ሲሉ ከኋላ ያለውን አሽከር ይወጋዋል ቤል ሽጉጥ ይተኩስና ጋረድን ሲገድለው የጋረድ ወንድም ቤልን በጦር ይወጋዋል አፄ ቴዎድሮስም የጋረድን ወንድም ይገድሉታል ጋረድንና ወንድሙን ጨርሰው ሲመለሱ ቤል ሙቶ ያገኙታል ራሳቸውን ይዘው ያዝናሉ።

አፄ ቴዎድሮስ።

እንዴት ብትወደኝ ብታስብልኝ

የላክልኝን ሞት ተቀበልክልኝ።

ከሩቅ የመጣ ነው ካገሩ ተሰዶ

ከእንግሊዝ አገር ከባሕሩ ማዶ።

ሲረዳኝ ሲመክረኝ እኔን ብቻ ወዶ

ሞቴን ተቀበላት ከፊቴ ተጋርዶ።

ከወንድም ከራስም አብልጦ ወዶኝ

ሊቀ መኳሱ ቤል ለኔ ሞተልኝ።

(ለአሽከሮቻቸው በቁጣ ቃል)።

የጋረድን ሰዎች ወገኖቹን ሁሉ

አንድም ሳታስቀሩ ሁሉንም ግደሉ።

ሬሳቸውንም እንዳትቀብሩት

እጅ እግራቸውንም በሴፍ ቁራጡት።

ባንድ ከምራችሁ ላውሬ እንድትሰጡት።

የታማኝ ወዳጄን የቤልን በቀል

በመቶና በሺ ብድሩ ይከፈል።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

መጋረጃ::

፬ኛ ትርኢት::

አፄ ቴዎድሮስ በዙፋናቸው ተቀምጠው በገና ይደረድራሉ::

(በአባ ግራኝ ምት)::

ክፉ ነው ይሉኛል ይሉኛል ጨካኝ (*)

ምክሬን ሳይቀበሉ ቃሌን ሳይሰሙኝ::

እኔ መዩ ቱርክ ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ?

አገራችን ሰፊ የተዋበች ለምለም

አይመለከታት አይመኛት የለም::

መጠንቀቅ አለብን አንድ ሆኖ መሥራት

ውድ አገራችንን ሌላ እንዳይወስዳት::

እኔ መዩ ቱርክ ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ?

አገር አንድ እንዲሆን ደካማ እንዳይባል

ሌት ተቀን ሲሠራ ሲጥር ሲታገል

ተንኮል ከመንገድ ላይ ቆሞ ያስተውላል

ምቀኝነት ክፋት ይዝቱበታል::

እኔ መዩ ቱርክ ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ?

ወንድሞቼ ሁሉ አውቀ ካልረዱት

ብቻውን ሲታገል በተስፋው ይሙት::

እኔ መዩ ቱርክ ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ?

ደግ ሲመክሯቸው ክፉ ያስባሉ

ቀናውንም ነገር ያወላግዳሉ

የተንኮልን ጥበብ በጣም ያጠናሉ

*አፄ ቴዎድሮስ ራሳቸው በገና መደደር ይወዱ እንደ ነበረና የእርሳቸውም ግትሞች ብዙዎች እንዳሉ የታወቀ ነው በሕይወታቸው ባሉና ከሞቱም በኋላ ከሕዝብ የተገጠሙላቸው ልዩ ልዩ ግጥሞች እንዳሉ የታወቀ ነው ነገር ግን የዚህ ቲያትር ደራሲ ራሱ ከጻፋቸው በቀር የሌሎችን ጣልቃ ማግባት ስላልፈቀደ በዚህ ቲያትር ውስጥ የሚገኙት ደራሲው የገጠማቸው ብቻ ናቸው::

እንደዚህ ለጥፋት ለምን ይጥራሉ?::

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

እኔ መዩ ቱርክ ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ?

አወይ ያገሬ ሰው ስማኝ ልንገርህ

መለያየት ትተህ ባንድ ካልሠራህ

ተንቀህ ተዋርደህ በገዛ አገርህ

ይመጣል ጨካኙ ባዕድ ሊገዛህ።

እኔ መዩ ቱርክ ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ?

ከንቱን ከቁም ነገር አውቀው ካልለዩት

ምግባርን ከሙያ ካላስተያዩት

ምን ይገኝበታል ይህ ከንቱ ሕይወት?።

እኔ መዩ ቱርክ ባይ የምሸሽ ነውኝ ወይ?

ቤቱን ተሸክሞ ጣራውን ይዞት።

ከስሩ የቆሙት አውቀው ካልረዱት

አቅም እያነሰው ሸክም በዝቶበት

ይወድቃል ምሰሶው ካልደጋገፉት።

እኔ መዩ ቱርክ ባይ የምሸሽ ነውኝ ወይ?።

(አንድ ባሕታዊ ከፊታቸው ቁሞ ይናገራል)።

ባሕታዊ።

መናኝ መነኩሴ ነኝ በበረሃ ኗሪ

የሰው ጎይል አልፈራም ያላንድ ፈጣሪ

ላለም የማልጓጓ እግዚአብሔርን ፈሪ።

ዓለም በቃኝ ብዬ ሄጃለሁ ሸሽቼ

ካባት ከዘመዴ ከሰው ተለይቼ።

ሱባዔ ገብቼ ስኖር በምናኔ

ዘወትር ሌት ተቀን ይታየኛል ለኔ።

በምትሠራው ግፍ በሕዝቡ ሥቃይ

በጣም ተቁጥቷል እግዜር ባንተ ላይ።

አሁን የመጣሁት ከእግዜር ተልኬ ነው

አቤቱታው በዝቷል ባንተ የሚሰማው።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

በጣም አብዝተሃል ግፍና ጭካኔ

ልብህ ዘንግቶታል መኖሩን ኵነኔ።

ከመሬት አንሥቶ ክብር ቢሰጥህ

አይጠረጠርም እንዲጠይቅህ

ለሕዝቤ ምን ሠራህ? ብሎም እንዲልህ።

በግፍ የፈሰሰ የንጹሓን ደም

አቤት አቤት ይላል እየጠራ ስም።

በቀድሞ ዘመናት ጨካኝ የተባሉ

ጃንጅስካን ታሜርላን አቲላ ሲባሉ።

እንዲሁም በሮሜ ኔሮን የተባለው (*)

ጨካኝ አረመኔ ስሙ የተጠራው

ትዕቢትና ጥጋብ ልቡና ነስቷቸው

እስካሁን ይነሣል በክፉ ስማቸው።

ስምህ እንደነሱ በክፉ እንዳይጠራ

ልብህን ምከረው እግዚአብሔርን ይፍራ።

እግዜር ነው የላከኝ እያልክ ስትል

ቱርክን ለማባረር ነግሠሃል ሲባል

የምታስጨንቀው ወገንህን ሆኗል።

ጉዳቷን አውቆላት እንድትሆናት ካሣ

በዋልከው ውለታ ስምህ እንዲነሣ።

እግዚአብሔር አስቦ ለውድ ኢትዮጵያ

አሟልቶ ቢሰጥህ ዕድልና ሞያ።

ጭካኔና ትዕቢት ሊኖርህ አይገባም

ሕዝቡንም ልትነሣው ዕረፍትና ሰላም።

*ኔሮን ክርስቲያን የፈጀ በጭካኔው ስሙ የተጠራ የሮማ ቄሣር ነው። ጀንጂስካን አቲላ ታርሜላን የተርታርና የሞንጉል ንጉሦች ናቸው አውሮፓንና እስያን ወረው ብዙ ጥፋትና ጭካኔ የሠሩ ናቸው።+

ሰውብ በግፍ መግደል ማቃጠል መንደር

ይህን ሁሉ እብሪት ሳትከፍለው አትቀር

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

እዜር ደግ ቢሆን ግፈኛን አይምር።

ለምትሠራው ግፍ ላለህም ጭካኔ (*)

የሚበቃ አይደለም ብትገባ ኩነኔ።

መወደድ ስትችል እንዲያው ትጠላለህ።

ለኢትዮጵያ የሰጣት የዘለዓለም ዕድል

በጠላቶቿ ላይ የሚያስገኝትም ድል።

የዳዊት በረከት በሳባ ተገኝቶ

ተከብሮ የሚኖር እስከ ዛሬ ጸንቶ

በንጉሦቹ ጀብዱ በደግነታቸው

ፍርድና ርኅራኄ ስላልተለያቸው።

ከመላው አፍሪካ ከእስያም ጭምር

አንዲት ኢትዮጵያ ክርስቲያን ብትኖር

ደርቡሽ እያበረ ሊያጠፋት ሲያስብ

አንተን የመረጠህ ከዚህ ሁሉ ሕዝብ።

ሕዝቤን ጠብቅልኝ ብሎ ቢልክህ

ኀይልና ተጠላህ እግዜር ራቀህ።

እንደዚህ እንዳንተ ከምድር የተነሡ

በእግዜር ደጋፊነት ካሰቡት ሲደርሱ

የነበሩትበት በቶሎ እየደረሱ።

አእምሮን ትተው በትዕቢት ሲመሩ

ከንቱ መና ሆነው ያለ ዋጋ ቀሩ።

*አፄ ቴዎድሮስ በብስጭት ዘመናቸው ብዙ ጭካኔ እንደሠሩና ሕዝብ እንዳለቀሰባቸው ታሪክ በሰፊው ይናገራል።

እንግዲህ ይበቃል ምክሩ ቢገባህ

አምላክ ይቅር ብሎ ልቡና ይስጥህ።

(ይሄዳል)።

አፄ ቴዎድሮስ (በቁጣ ቃል)።

ዐይኔ እያስተዋለ እንቅልፍ ሳይወስደኝ

ጋኔል እየመጣ በቀን የሚያቃዠኝ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

የተማሪ ተንኮል አንዳችም መተት ነው

እኔ አልደነግጥም ጉዳይም አልለው።

ይህን የምትሠራ ቄስና መንኩሴ (*)

በጣም ታስባለች እንድትጠፋ ነፍሴ።

መይሳው አይፈራም ቢመጣም ጋኔሉ

ተንኮል እያበዙ እናሳብድ ቢሉ።

በመርዝ በድግምት ሊገሉኝ ቢጥሩ

ብልሃትና ዘዴ ሁሉን ቢሞክሩ

ከእግዜርም ከሰይጣን ጥበብ ቢበደሩ

እኔን ለማሸነፍ ካለም ጋር ቢያብሩ

ምን ቢሆን አይችሉ ሐሳቤን ሊሰብሩ።

ይሻላቸው ነበር አርፈው ቢቀመጡ!

ከኔ ለመጋፋት አስበው ባይመጡ። ! (**)

ይሻላቸው ነበር ትእዛዜን ቢሰሙኝ!

ደግነት እያለኝ ጨካኝ ቢያደርጉኝ።

ተማሪም ባላገር ብትሆንም ባላባት

አልገዛም ካለች እኔ ከቶ አልምራት!!።

እንዳስመረረችኝ እሷም ይመራታል

መይሳው አይራራም አሳዶ ይፈጃታል!!

*በብስጭት ብዛት ማናቸውም ነገር የተንኮልና የጋኔል ሥራ ይመስላቸዋል።

** ጠባቸው ይልቁንም ከቤተ ክህነት እንደ ነበረ የታወቀ ነው።

መቼውንስ ቢሆን ማን ወዶ ይገዛል?!

ጎይልና ጭካኔ ሥልጣን ያስከብራል።

ማዘን መሳሳትም የከንቱ ፈሊጥ ነው

መጨከን መጨከን እስከ መጨረሻው!!

ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲሸቀጠቀጥ!!

መረፍ ነው መስቀልም እጅ እግሩን መቁረጥ!

አቤት አቤት ብሎ እስኪንቀጠቀጥ!!!።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

መጋረጃ::

፩ኛ ትርኢት::

ዐፄ ቴዎድሮስ ካፒቲን ካሜሮን መኳንንቶች::

አፄ ቴዎድሮስ::

ቱርኮች ቢያስቸግሩ ክርስቲያኖችን

እናንተን አድርጌ ወዳጆቻችን::

ንግሥትህን አምኜ ብጽፍላቸው

እንዴት ቢንቁኝ ነው ዝም ማለታቸው

መስሏቸው ይሆን እኔ እምፈራቸው

ትሕትናና ሰላም ስላሳየኋቸው?!::

እንዴት ላንድ ንጉሥ መልስ ይከለከላል

ለጻፈው ደብዳቤ እንዴት ዝም ይባላል::

በጣም ያሳዝናል እንዲህ ያለው ሥራ

ክርስቲያን ለሆነ በአልጋው ለሚኮራ::

አንተ ነህ ካሜሮን ይህን ያረግሽኝ

ቤልና ፕላውዲን እንዴት በረዱኝ (*)

ንግሥት ቢክቶሪያም ባላዋረዱኝ!

*ቤልና ፕላውዲን የአጼ ቴዎድሮስ ወዳጆች የነበሩ እንግሊዞች ናቸው:: ሁለቱም እርሳቸውን ሲረዱ ቀድሞ ሞተዋል::

ይሁን ከመሰለህ መልካም የሠራህ

እኔም አለቅህም ትታሠራለህ::

(ለገብርዬ)::

አንድም ነጭ ሳይቀር አቡነንም ጭምር

እመቅደላ ወስደህ በጥብቅ እንድታሥር!::

ካሜሮን::

በዓለም ሕግጋት በሠለጠኑት

አይቻልም ከቶ ቆንሲልን ሊያሥሩት::

ሕግ አይሰጥዎትም የሰው ዜጋ ማሠር

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ይህን ግፍ ሳይከፍሉት ምንም ቢሆን አይቀር።!

አፄ ቴዎድሮስ።

በገዛ አገሬ በያዝኩት መንግሥት

ምንም ብትቁጣ ያገርህ ንግሥት

ከቶ አይለወጥም የኔ ሕግጋት።

ካሜሮን።

ጎይለኛ ነች በጣም የኔኮ ንግሥት

እሷን የሚጠላ አለበት ግዘት

ክፉ እሚያስብባት ይጥፋ በመቅሰፍት

ይላል ማጎተሙ የእንግሊዝ መንግሥት። (*)

አፄ ቴዎድሮስ።

እርግማኑን ተወው ለኔ አያስፈራኝም

የፈረንጅ እርግማን በኔ አይደርስብኝም።

አውቃለሁ እንግሊዝ ጎይለኛነቱን

ግዛቱም በምድር ላይ ሰፊ መሆኑን

*Honi soit qui mal y pense የሚለው ነው

ባሕር ውቅያኖስ አልፎ መግዛቱን

ሻንቅላና ዐረብ ነጩንም ሕንዱን

መግዛቱን ዐውቄ የእንግሊዝ መንግሥት

ወዳጅ እንሁን ብዬ ጻፍኩኝ ለንግሥት።

ኢየሩሳሌምን ከቱርክ ለማዳን

እንችላለን ብዬ ከተረዳዳን።

በቅንነት ነበር እኔ የጻፍኩት

የሚገባ አይደለም እኔን ዝም አምለት።

ይህ ታላቅ ስድብ ነው ለሚገባውም ሰው።

ለኔ ብቻ አይደለም ለኢትዮጵያም ነው።

ባታውቁት ይሆናል የሕይወት ታሪኪነ

ክብሬን በመጠበቅ እዚህ መድረሴን።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ለክብሬ ታግዬ በክብር እኖራለሁ

ክብር ሳትለየኝ በክብር እሞታለሁ።!!

ካሜሮን።

የእንግሊዝን ቆንሲል እርስዎ ሲያሥሩት

መንግሥቱ ይሰማዋል እንዳዋረዱት።

ስለዚህ አይተውም ሳይመልስ ብድሩን

እንግሊዝ ክፉ ነው ለሚነካ ክብሩን።

አፄ ቴዎድሮስ (በቀኑታ ቃል)።

ክብሩን የሚያውቅ ሰው የሰው ክብር አይነካም

የፈቀደው ይሁን ማንንም አልፈራም።!!

(ለአሽከር)።

ውሰድልኝ ከዚህ ፊቱን አልየው!

እግዜር የተጣላው ክፉ ደፋር ነው።!!

(ካሜሮን ተይዞ ይሄዳል)።

መጋረጃ።

ክፍል ስድስተኛ።

(አዝማሪ ከመጋረጃ ውስጥ ሆኖ በዘለሰኛ ወይም መዲና ወይም በበገና ምት)።

መቅደላ መቅደላ አንቺ ክፉ ጦራ

ሴቱን ሁሉ ንቆ ሲኮራ ሲኮራ

ወንዱ አንቺን ወደደ ተኛ ካንቺ ጋራ።

ከቋራ ተነሥቶ ሲጋልብ ሲጋልብ

መቅደላ ላይ ቆመ ፈረሱ ገዝቶ ልብ።

ይምጡ ከየሜዳው ከጦራው ከወንዙ

ባይናቸው እንዲያዩት ተኝቶ ጦበዙ።

ሜዳው ሸለቆውም ተራራው ጫካው

አራዊት ሠራዊት ሰማይ ደመናው።

ምን ይሆን ነገሩ የተጨነቀው።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

መቅደላ አፋፉ ላይ ወድቋል አንበሳው

መቆሚያ ጠፍቶበት መሬት ብትከዳው

ትከሻ ባያገኝ የሚደገፈው

እጁን የሚጨብጥ ጠፍቶ እሚይዘው

ራሱን በራሱ ይዞ አሳረፈው።።

አፄ ቴዎድሮስ ፊታውራሪ ገብርዬ ደጃች ዓለሜ ባላምባራስ ገልሞ ወታደሮች በመቅደላ ምሽግ።።

አፄ ቴዎድሮስ።።

በግራም በቀኙም ባራቱ ማዕዘን

መድፎች አስጠምደን

ከወንዙ ሲደርሱ እንላቸዋለን።።

ገብርዬ በሯን ያዝ ጠብቅ በሰላምጌ

አንተ ደግሞ ዓለሜ ተሰለፍ ከራስጌ

ገልሞ ተከላከል ጠላትን ከግርጌ።።

እኔ ከመቅደላ ካፋፍ ስጠባበቅ

በርቱና ጠብቁ በጣም በመጠንቀቅ።።

ጠላታችን ብርቱ በጎይሉ የተመካ

ባሕር ውቅያኖስ ተሻግሮ የመጣ።።

በገንዘብ አባብሎ በጎይል አስፈራርቶ

እዚህ የደረሰው በኛ ሰው ተመርቶ።።

በዋላ አይመለስ ባላጋራችን።።

የእንግሊዝ ዝና ጎይለኛነቱን

እናንተም እንደኔ ስምታችሁታል

አረመኔ እስላሙን አስገብሮታል።።

ብዙ ትዕግሥትና ችሎታም አለው

አንዴ ያሰበውን ሳይፈጽም አይተውም።።

ሆኖም አንፈራውም ምንም ቢበረታ

በወሬ በዋላ እኛም አንፈታ።።

ዐሥራ ስድስት ዓመት ከኔ ጋር ያላችሁ

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

መቶ ሰባ ጊዜ ጦርነት ገጥማችሁ
እስከ ዛሬ ድረስ ድል እየነሣችሁ
ድል በድል ስትኖሩ በድል ያረጃችሁ።
አንድ ጊዜ ሳይታይ ጀርባችሁ ለጠላት
በክብር ያደጋችሁ ውርደትን ሳታውቁት ።
እንኳንስ እንግሊዝ ቢጣላን ዓለምም
ከቶ ምንም ቢሆን እጃችን አይያዝም።
ጠላትም አይገባ ሳይፈስ ደማችን
መሞት ይገባናል ሳይነካ ክብራችን።
እኔም እንደ ወትሮው አለሁ አብሬያችሁ
ለማንም አልገብር እኔ ንጉሣችሁ።
ምቀኛ በዝቶብኝ ሥራዬንም ቢያውክ
በኔ ላይ ታድሞ እንግሊዝም ቢላክ
ልጄም ያሳደግሁት ቢሄድም ምኒልክ።
ተጽፎልኝ እንደሁ መቼም አይቀርልኝ
ክብሬን ሳላስነካ መሞት ብቻ አለብኝ።
ወይ ፊት ልገዛ የተጻፈ ካለ
አይጠረጠርም ተፋ በድል አለ።
ዋና ቁም ነገሩ ልብ ላለው ሰው
ዕድሉን ማመን ነው መኖር በተስፋው።
ድል የእግዚአብሔር ነው እሱ ለሰጠው
ከቶ የማይቀር ነው አንዴ የጻፈው።
ስለዚህም አሁን እንጋደላለን
በተስፋና በምነት እናሸንፋለን።

ፊ/ ገብርዬ።

ጌታዬ ያምድጡኝ ሐሳቤን ልናገር
እስከ ዛሬ ድረስ ስንዞር አገር ላገር።
ድል በድል አግኝተን ሁሉን አሸንፈን

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

በመላው ኢትዮጵያ ተከብረን ተፈርተን

ለውጭ አንገብርም በድል እንሞታለን

ምቀኞች ተማክረው ጠላት ቢለቁብን

ሁሉም አድማ መትተው ቢተባበሩብን።

በኋላ ይቆጫሉ በጣሙን ያዝናሉ

በገዛ ራሳችወ ዘለዓለም ያፍራሉ።

እኛ ግን ለመሞት ጥቂትም አንፈራ

ትውልድ ሲገምት ያቀድነውን ሥራ

አይጠረጠርም በኛ እንደሚኮራ።

ደ/ ዓለሜ።

እስካሁን የረዳን እግዜር ያውቅልናል

ውርደት ከመቀበል መሞት ይሻለናል።

ባላባት መሳፍንት ነጋሢ የተባሉ

በትግሬ በላስታ በጐጃምም ያሉ።

ዘውዳችንን ቀማን ብለው የሚቆጩት

በባዕድ አዙረው በቀል የሚወጡት።

አሁን ባይታያቸው የክፋት ሥራቸው

ጠላት አሳልፈው በኛ መልቀቃቸው

ታላቅ ክህደት ነው የሚያስወቅሳቸው።

ተስማምቶ ለመኖር እነሱ ሳይችሉ

እርስ በራሳቸው አሁን ይዋጋሉ።

አንድ ያደረግነውን በመለያየት

አገሩ ሲዳከም ይመጣልም ጠላት

ይገባዋል ብሎ በባዕድ መገዛት።

አፄ ቴዎድሮስ።

ንግግራችሁን አዳመጥኩት በጣም

የንዴትም ቢሆን ቁም ነገር አያጣም።

ለመቀበል ሲሉ አገርን መካድ ፤

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ከጠላት ተስማምቶ ባንድነት መሄድ

ምንም ቢበሳጨ አይሆንም መንገድ።

(ከፍ ባለ ድምፅ)።

እንግሊዝም ይምጣ ዘኖኑን አስጭኖ

መይሳው አይሸሽም ይዋጋል ጨክኖ።

አይሂችሁ ጐበዞች እንግዲህ ቁርጥ ነው

ባንድ ልብ ሆነን ከመጣም እንበለው።

የቋራ ያታክልት፤ የጐርጐራ ጀግኖች

በጐጃም በወሎ በሸዋ አሸናፎች

በትግሬ በላስታ ሁሉን ድል አድራጐች።

ስማችሁ ተጠርቷል በመላው ኢትዮጵያ

ለእንግሊዝ አሳዩት ያላችሁን ሙያ።

መሞት ያውቅላ በሉት የኢትዮጵያ ሰው

ለክብሩ ላገሩ ላበላው ጌታው

ጮማ ለሚያበላው ጠጅ ላጠጣው።

ሺህ ጊዜ ሞት አይቶ ሞትን የማይፈራ

በድል አድራጊነት ስማችን ሲተራ።

ሽሽትን ፍርሃንት አይተናት አናውቅም

ከቶ ምንም ቢሆን ለውጭ አንገርብርም

በድል በድል አግኝተናል ያለድል አንለቅም።

በጥበብ በዘዴ ፈረንጆች ቢበልጡን

በመሣሪያ ብዛት በጎይል ቢጫኑን

የጀግንነት ሙያ አበሾች ብዙ አለን

ላገር ለክብራችን መሞት እናውቃለን።

ንጉሡን አገሩን የሚወድ ከልብ

ሞትን የማይፈራ ወንድነት ያለው ሕዝብ።

ለክብሩ እሚሠጋ የሚሳሳ በጣም

አይኖርም ተዋርዶ ለባዕድ አይገዛም።!

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

መጋረጃ::

፪ኛ ትርኢት::

(የሽለላ የመድፍ የጠመንጃ ተኩስ ድምፅ ይሰማል አፄ ቴዎድሮስ እየተንቁራጠጡ በመነጽር ያስተውላሉ ዓለሜ እየሮጠ ይገባል)፡

አፄ ቴዎድሮስ፡፡

ከምሽጉ ጫፍ ላይ በመነጽር ሳይህ

በጫካው መካከል ታይቶኛል ፈረስህ

በጥድፊያ በግልቢያ ስትመጣ ወደዚህ፡፡

ባኂኂንህና ባይንህ የሚታየኝ

በጣም የደነገጥክ ያዘንክም መሰለኝ፡፡

ተናገር ዓለሜ ምንም አትደብቀኝ

የሆነውን ነገር እባክህ ንገረኝ፡፡

ደ/ ዓለሜ፡፡

የግርማዊነትዎን ትእዛዙን አክብረን

በእሮጌ ሽለቆ ዛሬ ጧት ወርደን፡፡

ጠላት ሲጠብቀን በምሽግ በሠልፍ

ቁልቁለቱን ስንወርድ ተኩሰብን መድፍ፡፡

እሳተ ገሞራ ጥይት ዘነበብን፡፡

እኛም በነፍጣችን እየተታኮስን

ተንደርድረን ወረድን እየተሠገሥን፡፡

ጠላት አስቀድሞ ምሽጉን አስክቦ

መድፍና ጠመንጣ ግንቡን አስከብቦ፡፡

እንደ ድንጋይ ናዳ ከላይ ስንመጣ

መድፉም እያጓራ ጥይቱ ሲንጣጣ፡፡

ሰዋቸውን ተፏክሮ ቁልቁል ሲንደረደር

በካብ ተከልሎ ሲያዘንብበት አረር

አልታገድ ብሎ የርስዎ ወታደር

ካቡን እየጣሰ ገባ ከመአክከል፡፡

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

በሳንጃና በነፍጥ ጠላት ሲከላከል።

ድብልቅልቅኑ ሆኖ ሞት በጣም ረክሳ

በዙሪያችን ሁሉ ተረፍርፎ ሬሳ።

ጠላት ተስፋ ቁርጦ መድረሻውን አጥቶ

በብዛት ተጫነን ትኩስ ጦር አምጥቶ።

ያን ጊዜም ልባችን ተስፋውን ቁረጠ

ደፋሩም ገብርዬ በጣም ደነገጠ።

ተው በለው እያለ ሰዉን ሲያበራታ

ጐራዴውን መዞ ግራ ቀኝ ሲማታ።

ሰውነቱ ሁሉ ደም አቧራ ለብሶ

ግንባሩን ቢመታው በሩቁ ተኩሶ።

በርቱ ይደርሳሉ አይቀሩም ጌታዬ

እያለ ሲናገር ወደቀ ገብርዬ።

አፄ ቴዎድሮስ።

ይበቃል እንግዲህ ተወኝ በቃ ዓለሜ

አሁን ተረዳሁት ያየሁትን በልሜ።

ገብርዬ ተሞተ ምን ተስፋ አለኝ እኔ?

ገብርዬ ገብርዬ የጦር መኰንኔ

አሸክር አይደለህም ጓደኛ ነህ ለኔ።

አሥራ ዘጠኝ ዓመት አንዴም ሳትለየኝ

ምነው በጦር ሜዳ እንዲህ አጋለጥከኝ።?

እስከ ዛሬ ድረስ ትእዛዜን ስታከብር

ዛሬ ቀድመኸኝ ሄድህ በጣም ብትዳፈር

ስታጅበኝ ኖረህ ስትከተለኝ።

የለም አይመስለኝም አንተ የከዳኸኝ።

አስበህ ይሆናል ልትይዝልኝ ቦታ

መምጣቴን አውቀኸው የማታ የማታ።

ደ/ ዓለሜ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ተስፋ ቢጠፋ ነው የመረጠው ሞቱን

ጠላትን እያየ እንዳይመልስ ፊቱን።

እንደ ኮራ ሞተ ሳያስነካ ክብሩን።

እኛም እንከተል ካሳየን መንገዱን።

ገብርዬ ከሞተ ሰዋችን ካለቀ

ምንም ተስፋ የለን አለቀ ደቀቀ።

በገደሉ አፋፍ ላይ እንጠባበቀው

አንድ ለሺም ቢሆን ዝም ብለን አንለቀው።

(እቴጌ ጥሩ ወርቅ ይገባሉ)።

እቴጌ ጥሩ ወርቅ።

ጦራችን ድል ሆኖ መበተኑንና

ገብርዬም መሞቱን እውነተኛ ጀግና።

ወታደር ነገረኝ ከሞት የተረፈ

መላላክ ይሻላል አንዴ ካሸነፈ።

እስረኞቹን ይስጡት እርቁም ይደርደር

ምንም ተስፋ የለን የሚያግደርድር።

ደብዳቤ ይጻፍለት አሳቡን ይናገር

ዓለሜ ይሂድና ለኛ ይከራከር።

አፄ ቴዎድሮስ (በማመንታት)።

ይሁን አንቺ እንዳልሺው ዓለሜ ይሂድ

መሸነፍን ማመን በውድም በግድ

የማይቀር ዕዳ ነው ለሚከዳው ገድ።

ሰላማ ላንተ ይሁን ብሎ ይጻፍና

ዓለሜ ውሰድለት ከብትም ጨምርና

መልሱን ተቀብለህ ወደዚህ ቶሎና።

(ዓለሜ እጅ ነሥቶ ይሄዳል)።

እቴጌ ጥሩ ወርቅ።

ዛሬ በፋሲካው በትንሣኤው ቀን

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ክርስቲያን ሲደሰት እኛ ተጨነቅን።

እንግሊዝ አይደለም ዛሬ ያሸነፈን

ግልጽ ነው ነገሩ እግዜር ነው የጣለን።

እኔም ብዙ ጊዜው ነግሬዎታለሁ

እግዜር እንደ ጠላት ተረድቼዋለሁ።

ግፍ እብሪት ጭካኔ በጣም ስላበዙ

ፍርድን በማጓደል በግፍ ስለ ገዙ፡

ከምድርም ከሰማይ በጣሙን ተጠሉ

አይጨክንም ነበር ባይበዛ በደሉ።

አሁንም ልብዎን ወደሱ ይመልሱት

እርሱ መሓሪ ነው ይቅርታ ይለምኑት።

አፄ ቴዎድሮስ።

ከድኅነት አውጥቶ ዘውድ ቢሰጠኝ

አልገዛም ላሉት በጣም ጨከንኩኝ።

ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሊኖር ባንድነት

ቀጥሩም እንዲበዛ የክርስቲያናት

ኢትዮጵያን ደርቡሽ እንዳያጠፋት

ኢየሩሳሌምን ነጻ ለማውጣት

ይህ ነበር ጥረቴ የልቤ ምኞት።

አሳቤ እንዳይፈጸም ለተቃወሙኝ

ጥቂትም አልሳሳሁ በጣም ጨከንኩኝ።

አንቺ እንደምትይው የሚረዳኝ ቢሆን

ባልቸገረኝ ነበር ለሱ ታዛዥ መሆን።

ግን ልቤም አያምን ይረዳኛል ብሎ

ሥቃይ ሳያበዛ በገደለኝ ቶሎ።!

እቴጌ ጥሩ ወርቅ።

የልብዎን ምኞት ተረድቼዋለሁ

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ብርታት በቅንነት እንዳለው አውቃለሁ።

ምኞትም ያማረ ልብም ቢሆን ቀና

እግዜር ካልደገፈው መቼም አይቃና።

በወጠኑት አሳብ ስምምም ይጠራል

በመጭ ትውልዶች ሲከበር ይኖራል።

የምድሩ አያሠጋም ዋናው ነው የላይኛው

እንበርከክና ማረን እንበለው።

እሱ ቂም አያውቅም ምን ጊዜም መሓሪ ነው።

(እቴጌ ጥሩ ወርቅ ተንበርክከው ይጸልያሉ አፄ ቴዎድሮስ አጠገባቸው ቁመው ይተክዛሉ)።

እቴጌ ጥሩ ወርቅ።

ፈጣሪ አምላኬ ሁሉን የምትችል

ሁል ጊዜም አንተ ነህ የምታገኝ ድል።

ትዕቢት ልባችንን ቢያደርገው ተራራ

ቁጣህን ላንችለው በከንቱ ስንኮራ

እንጨነቃለን ሲመጣ መከራ።

አምላክ ይቅር በለን ለሠራነው ግፍ

እኛን ብትጠላ ኢትዮጵያን ደግፍ።

እኛን ስትቁጣ እሷን አታጥፋት

ከመጣባት ጠላት አንተው አዳንት

እስከ ዛሬ ድረስ እንደ ጠበቅኻት፤

እስከ ዘላለሙ እንዳትለያት።

እጆዋን ወደ ሰማይ እየዘረጋች

አምላኬ አምላኬ ማረኝ ትላለች።

እርዳታ አትፈልግም ከሰዎቹ ዘንድ

እምነቷ ባንተ ነው አንተን የምትወድ።

(ዓለሜ ከውጭ ይገባል)።

አፄ ቴዎድሮስ (በችኮላ አነጋገር)።

ታድያስ ምን መለሰ እንግሊዝ?

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ዓለሜ።

እሱ እሚጠይቅ እጅዎን እንዲይዝ።

አፄ ቴዎድሮስ (በቁጣና በምሬት)።

እንዴት ብሎ አሰበ ለመያዝ እኔን እጅ!!

አይማረክም በለው መዩ ያንበሳው ልጅ።!

እንዲህ ያለውንም ደፍሮ መጠየቁ

መገመት ባይችል ሰው ባለማወቁ።

እስከ ዛሬ ድረስ በደል ተመርተን

ተከብረን ተፈርተን ስንገዛ ኖረን

እግዜር ተለይቶን ዛሬ ቀን ቢጐድል

ከባለዕድል ገጥመን ቢበልጠንም በድል።

አይፈቀድለትም እንዲማርከን

አንኖርም ከቶ ባለም ተዋርደን።

ንገረው ለእንግሊዝ የልቤን አሳብ

እኔን ለመማረክ ጭራሽ አያስብ።

ጥያቄም ማቅረቡ ለኔ ስድብ ነው።

በኢትዮጵያ ታሪክ ከመገመሪያው

ንጉሡ ሲማረክ ማንም አላየው።

ይህ ከጥንት የቁየ የክብር ልማድ

መጠበቅ አለበት ለኢትዮጵያ ዘውድ።

ዓለሜ ንገረው በጣም አስጠናው

አይማረክም በለው ሳይሞት አንበሳው።!!

ለማንም አይገብር ካሣ መይሳው!

ኢትዮጵያን በሙሉ ቀጥቅጦ የገዛው

ስንት ጐበዝ ጀግና አባሮ የያዘው

አይጨበጥም እጁ ይፋጃል በለው።!!

(እቴጌ ጥሩ ወርቅ ዓለሜ፥ ገልሞ ሌሎች አርበኞች ብዙም እስረኞች ተሰብስበዋል የመድፍ ተኩስ ይሰማል)።

አፄ ቴዎድሮስ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

እንታረቅ ብዬ ብልከው ዓለሜን

እንግሊዝ አሰበ ሊጨብጠው ክንዴን።

እኔ አልማረክም እጇን አላስይዝም

አላስነካም ክብሬን ጠላት አይገዛኝም።

ከምርኮ ከውርደት መርጫለሁ ሞቴን

እናንተም አደራ ሚስቴንና ልጇን።

(የተኩስ ድምፅ ይቃረባል)።

ለመጭዎች ትውልድ አስጠንቅቁ ልመ-ት

ገልሞ አንብብላቸው ኑዛዜን ይስመ-ት።

(ወረቀት ከኪሳችወ መዝዘው ይሰጡታል)።

(ገልሞ ያነባል)።

በጐንደር በጐጃም በትግሬ ያላችሁ

በላስታ በወሎ በሸዋም ያላችሁ።

ከሕንድ ውቅያኖስ ምጽዋ ድረስ።

ከደቡብ ሻንቅላ ነጭ ዓባይ መለስ።

የነአብርሃ አጽብሃ የነዘርዓ ያዕቆብ

የነፋሲል አገር ኢትዮጵያ ሕዝብ

ክርስቲያን እስላሙ ባንድ ተሰብሰብ።

አንድ እንድትሆን ነው ስታገል የሞትኩት

ኢትዮጵያዊ ሁሉ ይኸንን ተረዱት።

ያገሬ ሕዝብ ሁሉ በጣም ተባበር

ነፃነትክን ጠብቅ ለውጭ አትገብር

ስንፍና አስገብተህ እንዳታጣ ክብር።

ለሚያልፈው ለከንቱው ብዙ አትስገብገብ

ለትውልድ ውለታን ለመተው አስብ።

ኢትዮጵያዊ ሁሉ እስላም ክርስቲያን

ካንድ እናት ተወልደን ወንድማማች ነን

ምቀኝነት ቅናት መናናት ትተን

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ተከብረን ተፈርተን ምስጉን እንሁን።

ላገር ለትውልዱ ቁም ነገርን ሥሩ

ባንድ አሳብ ባንድ ልብ ሁል ጊዜ ተመሩ።

አገር ለሚያኮሩ ላገር ለሚሠሩ

ድጋፍ ሁኑ እንጂ እንቅፋት አትሁኑ።

መመቅኘት ማወክም ጠላትን ነው እንጂ

አይቀናም ከቶ በገዛ አገር ልጅ

ለራስ ብቻ ማሰብ ለማንም አይበጅ።

ባለሙያ ሲገኝ ለኛው ያኰራናል

ጥቅሙም ሆነ ክብሩ ለኛው ይተርፈናል።

ስማኝ አደራህን አድምጠኝ አገሬ

ጐጃም ሸዋ ጐንደር ወሎም ሆነ ትግሬ።

አንድነትክን ጠብቅ ልብህም ከፍ ይበል

ባዕድ እንዳይገባ ትውልድ እንዳይበደል።

መከራ ፈተና አለህ ብዙ ድካም

በቅን ለሚሠራ እንቅፋት አይጠፋም

ሀብት ንብረት ያለው ምቀኛ አያጣም።

ለዚህ መድኅኒቱ ልብን ማጠንከር

ክብርን ሃይማኖትን ጠብቆ መኖር።

ታሪክን ትውልድን የሚያስብ ከልቡ

ከመንገድ አይቀርም ይደርሳል ከግቡ።

ለመሪዎቻችሁ አስቸጋሪ አትሁኑ

በእምነት በሃይማኖት ሁኑ ልበ ጽኑ።

ላገር ለክብራችሁ ምን ጊዜም ታገሉ

ጊዜን በመከተል እንዳትዋልሉ።

ስንፈት እንዳይገባን እንዳይገዛን ባዕድ

እምነትን አጽንቶ መጓዝ ባንድ መንገድ

ላገር ጥቅም ለክብር ልቡናን ማስገደድ

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ይህ ነው አስፈላጊው ወደ ፊት ለመሄድ።

አገርን ንጉሥን ደግሞም ሃይማኖት

ምንም ቢበድሉ አይገባም መክዳት።

በጎ ሲሠሩለት የማይረዳ ሕዝብ

ሙያና ተግባርን የማያውቅ ልብ።

ልፋትን ድካምን ዐውቆ የማይረዳ

በመጨረሻውም አጋልጦ እሚከዳ

ለትውልድ ያተርፋል የውርደትን ዕዳ።

ይህ የደረሰብኝ ፈተና ክህደት

ኋላ ለሚመጡት ይሆናል ትምህርት

ምክሬን ተቀበሉኝ አሳቤ ይግባችሁ።

ታግዬ ታግዬ ይኸው ሞትኩላችሁ

ጠላት አይዘኝም እኔ ንጉሣችሁ።

ገልሞ።

እንግዲህ ካለቀ ተስፋ ከጠፋብን

እስረኞቹን ገድለን መሞት ብቻ አለብን።

በሰይፍ ቁራርጠን ገደል እንጣላቸው

ንዴትን በቀልን እንወጣባቸው።!!!

አፄ ቴዎድሮስ።

አገር አንድ እንዲሆን አስበን ባቀድነው

እስከ ዛሬ ድረስ ሕዝቡን አስጨነቅነው

ጎይልና ጭካኔ ብዙ አሳየነው።

እንዴት ከሞትን ወዲህ ለእብቀል እንስጠው።?

ተወኝ በቃ ገልሞ እግዜር ተጣልቶናል

ክፉ ሳንሠራ ብንሞት ይሻለናል።

እስረኞቹን ሁሉ በሉ ልቀቋቸው

ሁሉም በነፃነት ይግቡ ካገራቸው።

አንድ እስረኛ።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ልቀቃቸው ብለህ አሁን የምታዘው

ቢጨንቅህ ነው እንጂ መቼ ወደህን ነው።!

እስከ ዛሬ ድረስ ስትጫወትብን

አሁን ትቀጣለህ አገኘህ ብድርህን።!!

አዒ ቱዎድሮስ።

እንዴት ብለሽ አንቺ እንዲህ ታስቢያለሽ!

ምሕረት ባደርግልሽ የፈራሁ መሰለሽ።?

እንግሊዝ ቢያሸንፍ ዕድሌ እምቢ ቢለኝ

በቀሌን ለመውጣት አሁም ጊዜ አለኝ

በል እጅዋን ጕትተህ ገደል ጨምርልኝ።!!

(ገልሞ ጕትቶ ከገደል ይሰደዋል)።

ሸዬ ዘረፉ።

ጌታዬ ይማሩን እሱን አያድምጡ

አንዱ ስላጠፋ ሁሉም አይቅጡ።

በዚህ በክፉ ቀን ምሕረትን ሲሰጡ.....

አጼ ቱዎድሮስ። (በችኮላ አነጋገር)

በሉ እናንተ ሂዱ በገደሉ ውረዱ

መጡ ተቃርበዋል ሳይሟችሁ ሂዱ።!!

ገልሞ (እንባውን እየጠረገ)።

በቅና ተለያየን አወይ የኔ ጌታ

እስከ ዛሬ ድረስ ፈረስህ ሳይገታ።

መሬት ብትከዳህ ብቻህን ቀረህ።?

እኔ አልለይህም ጌታዬ እኮ ነህ።

ሥቃይህን አላይም እሞታለሁ እኔ

ከቶ ሌላን ገዥ አያየውም ዐይኔ።

ጥይት አለኝ ድረስ ተኩሼ ተኩሼ

ደግሞም በጕራዴ በጦርም መልሼ።

እስክትወጣ ነፍሴ እኔ እጋደላለሁ

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ጌታዬ ስትሞት ወዴት እቀራለሁ።።

(እየሸለለ ይወጣል)።።

ስንቱን ጋራ ወጥቶ ስንቱን ሜዳ ሲያልፈው

የመቅደላን ዳገት ለመውጣት አቃተው

በቃኝ ልረፍ አለ ዓለም ቢታክተው።።

በጐጃም በላስታ በትግሬ ተባረን

በወሎ በሸዋ ስንሄድ ኖረን

ታክተን ዓለሙ ዛሬ ዕረፍት አማረን።።

ወንድ ልጅ መውለዷ ደስ አላት እናቱን

ማንም አልነገራት መከራውን ሞቱን።።

ዕድል ከተቃና ይገኛል ታማኝ

በክፉ ቀን ብቻ ወዳጅ አይገኝ።።

በጌታው በንጉሡ ያኖረው እምነት

ዕድሉን ዕጣውን በርሱ ጥሎበት

ተለይቶ አይቀርም ቀን የከዳለት

ጮማውን የበሉት ጠጁንም የጠጡት

ቁርጠኛው ሲመጣ እንዲህ ካጋለጡት

ራሱን ተማምኖ እንደ ኮራ ይሙት።።

ሙያ ምን ያደርጋል ምን ይረባል ዕውቀት

ዕድል ያስፈልጋል ዋጋ እንዲገኝበት።።

ላገሩ ሲሠራ ቀንና ሌሊት

ሁሉም ችላ ብለው ብቻውን ተውት

በቃኝ ልረፍ አለ አንበሳው ደክሞት።።

****

፫ኛ ትርኢት።።

አፄ ቴዎድሮስ።።

ካፋፍ ላይ ቆሜ አገሬን ልየው

በቃ ተለያየን ልሰናበተው።።.....

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

(ከፍ ካለ ቦታ ላይ ቁመው ያስተውላሉ)።

ያው በስተቀኝ ሸዋ ይፋትና መንዝ

በሩቅ ይታያል ጋራው መገዘዝ።

ይኸው ከታች ወሎ

ከግርጌ ተንጣሎ።

ዋድላና ደላንታ በጣም የታወቁ

ፊት ለፊትም ትግሬ ይታያል በሩቁ።

ዋግ ላስታ በጌምድር አማራ ሳይንት

የጐጃም አቅጣጫው ቅርብ ነው ሲያዩት።.....

(በትካዜ)።

ይኸን ሁሉ አገር ስንቱ ረገጥኩት

አንድ እንዲሆን ነበር እኔ የደከምኩት።

የታል የበቀለው የዘራሁት ሁሉ?

ምድረ በዳ መስሏል ሰዎችም የሌሉ።

አስቤልሽ ነበር በጣሙ ከልቤ

አንስማማም አሉ ልጆችሽ ካሳቤ።

ምኞቴን ሳልፈጽም ዕድሌ እምቢ ካለ

ይግዛሽ ኢትዮጵያ ከኔ የተሻለ።

እኔስ እሞታለሁ ክብሬን ሳላስነካ

ዕድላሙን ይስጥሽ በኔ የሚተካ።

ከክፉ ያድንሽ እስከ ዘላለሙ

ተራራ ሸለቆሽ ሁል ጊዜ ይለምልሙ።

ዘላለም ልጆችሽ ተባብረው ይኑሩ

ዘላለም ተከብረው ዘላለም ይፈሩ።

ከምቀኛ ጠላት እግዜር ይጠብቅሽ

ከመለያየትም ሁል ጊዜ ያድንሽ።

ኢትዮጵያ አገሬ እንሽ ምድረ ገነት

ማንም አይደፍርሽም የወንዶች እናት።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ደኅና ሁኚ ኢትዮጵያ ሀገር ሰላም

ኑሪ በነፃነት እስከ ዘላለም።

(የመድፍና የጠመንጃ ተኩስ ጩኸትም እየተቃረበ ይሰማል ገልሞ ሲፎክር ይሰማል የገልሞ ፊከራ)

ቋራ ላይ ገዳይ ድንጋይ ለድንጋይ

ጉርጉራ ገዳይ በየሜዳው ላይ።

በሸዋ ገዳይ ዋሻ ለዋሻ

የንጉሥ ወታደር የጦር ወጌሻ።

የታጠቅ አሸከር የባለ ዘውዱ

መግደል መማረክ የዕለት ልማዱ።

(ድምጡ እየተዳከመ የዚያ ተኩስ እየበረታ ሲሄድ ይሰማል)።

አፄ ቴዎድሮስ (ሽጉጣቸውን መዘው)።

አንተው ከሰጠኸኝ አንተ ከነሳኸኝ

ውርደት ከመቀበል ራሴን ልግደላት

አምላክ ይቅር በለኝ ላደረግሁት ጥፋት

ፈቃድህ ይፈጸም ነፍሴን ተቀበላት።

(በሽጉጥ ራሳቸውን ይገድላሉ)።

(የእንግሊዝ ወታደሮች ወዲያው ይደርሳሉ ጀኔራል ናፒዬር በኋላ ይመጣል ራሳውን አልብሰው በዙሪያው ይቆማሉ ካሜሮን መጥቶ ራሳውን ያይል)።

፬ኛ ትርኢት።

ጀኔራል ናፒዬር (በትካዜ አነጋገር)።

ትልቅ ሰው ነበረ ይህ የወደቀው

የሚያስደንቅ ሙያ ብዙ ነበረው።

ጭካኔና ኩራት እንደዚህ ጣለው።

ያባቶቹን ታሪክ ጠብቆ ሳይረሳ

አይማረክም ብሎ የይሁድ አንበሳ።

በገጃ እጁ ሞተ እንዳይነካው ውርደት

እንዲህ ያለ ጀግና መከበር አለበት።

ትዕግሥትን ትቶ በኀይል ሲሠራ

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

ራሱን ተማምኖ በራሱ ሲኮራ

እንደ ኮራ ሞተ ተከብሮ ሲፈራ።

(እቴጌ ጥሩ ወርቅ እያለቀሱ ይገባሉ ልጃቸው ተከትሏቸዋል)።

እቴጌ ጥሩ ወርቅ (በቅልሶ ዜማ)።

አዬ ጉድ አዬ ጉድ አወይ የኔ ጌታ

እምቢተኛን ሁሉ ሲቀጣ ሲመታ።

የሚመታው ቢያጣ ዛሬ ራሱን መታ።

..... አወይ የኔ ጌታ።

በትግሬ በጐጃም በሸዋም ያላችሁ

አንበሳው እንዲያዝ ብዙ የደከማችሁ

እሱ ራሱን ይሏል አትፍሩ በቃችሁ።

..... አወይ የኔ ጌታ።

አያችሁልኝ ወይ ይህን ዐይነት ግፍ

ተገዝን ተገዝን ስንደርስ ካፋፍ

እኔ ሴቷ ቆሜ ወንዱ ደክሞት ሲያርፍ።

..... አወይ የኔ ጌታ።

ብመክርህ ብመክርህ አልሰማም ብለህ

ከምትወደው ልጅህ ካለም ተለየህ።

..... አወይ የኔ ጌታ።

ይበላናል ብሎ ዓለሙ ሲሠጋ

አንበሳው መቅደላ አላገኘም ሥጋ።

በጣም ሆዳም ነበር ሁል ጊዜ ራብተኛ

የሚበላው አጥቶ እንደራበው ተኛ።

..... አወይ የኔ ጌታ።

አሞራ አንጃበበ ልማደኛ ነው

እስከ ዛሬ ድረስ ሰብሮ ሲያበላው

ዛሬስ ተዳከመ ጉልበት አነሰው፤

ሥጋ አልበላም ብሎ ጥይቱን ጠጣው።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

..... አወይ የኔ ጌታ።።

ይብላኝ ይብላኝ ለኛ እዚህ ለቀረነው

አንተማ ምን አለ በጅተህ ወጣኸው (በጅህ ተወጣኸው)።።

.....

፩ኛ ትርኢት።።

ጀኔራል ናፒዬር።።

እንለለፍና ሰላምታ እንስጠው

እጓለ አንበሳ ቴዎድሮስ ንጉሥ ነው።።

(ጥሩንባ ይነፋል ሰላምታ ይሰጣሉ)።።s

ወገኖቻችንን ነፃ ካወጣን

እንሂድ እንግዲህ ሕዝቡ ሳይጣላን።።

ያፄ ቴዎድሮስን ልጅ በክብር እናኑረው (*)

አገራንች ወስደን ጥበብ እናስተምረው።።

ዘውዱንም አክብረን እናቀምጠው።።

አገርና ክብርን ወዶ ለሞተው

ዘውዱን እኛ ወስደን ከቶ አናቀረው።።

ምግባርና ሙያ እንግሊዝ ያከብራል

ኋላም ለሚነግሠው ዘውዱን ይመልሳል።።

ዘውዱንም መልሶ የሚያመጣው ንጉሥ (**)

ምስጋና ያገኛል ክብርን በማስመለስ።።

መጋረጃ።።

ተፈጸም ።።

*ያፄ ቴዎድሮስ ልጅ ዓለማየሁ ቴዎድሮስ እንግሊዝ አገር ቂይተው በወጣትነት ዕድሜያቸው እዚያው ስለ ሞቱ በእንግሊዝ መስፍኖች መቃብር በክብር ተቀብረዋል።።

** በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን በነበሩ ጊዜ ሎንደን ሄደው የአፄ ቴዎድሮስን ዘውድ መልሰው አምጥተውታል።።

ስለ ዐፄ ቴዎድሮስ በዘመናቸውና ከሞቱም በኋላ ከሕዝብ የተገጠሙላቸው ብዙዎች ግጥሞች እንደሚገኙ ይልቁንም በበገና የታወቁ ናቸው።። ስለዚህ አንዳንዶቹን ለመታሰቢያ ያክል ከቴያትሩ መጨረሻ አገባኋችወ።።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

(በሞቱ ጊዜ የተገጠመ)።

አንበሳው መቅደላ ተኝቶ አየሁት

ሰው እያዩ መሸሽ ነውር ሆኖበት።

መቅደላ አፋፉ ላይ ጪኸት በረከተ

የሴቱን አላውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ።

የትግሬንም ንጉሥ የሸዋንም ንጉሥ ሲንቁ ሲንቁ

የጐጃምን ንጉሥ የላስታንም ንጉሥ ሲንቁ ሲንቁ

ወንድ ያለራስዎ ገድለውም አያውቁ።

እኔ ብቻ ልግዛ ነውና እንገሩ

እዚያ ላይም ሄደው እንዳያስቸግሩ።

ዳር እስከ ዳር ይዞ የገዛው ንጉሥ

እንዲህን ለሱ ነው ጥይት የሚጮርስ

ዳማ ጉራች ቡሎ የቴዎድሮስ ፈረስ

አንድ ጥርኝ ሆነ መቅደላ ሲደርስ።

መላው የጐጃም ሰው መላው የትግሬ ሰው ተይዞ በምጥ

የእንግሊዝ ሐኪሞች መጥተው ቢይዙት

ተገላገለ አሉ ይህ ሁሉ ፍጥረት።

ገደልን እንዳይሉ መሥተው አገሯቸው

ማረክን እንዳይሉ ሰው የለ በጃቸው

ምን አሉ እንግሊዞች ሲገቡ አገራቸው።

ለወሬ አይመቹም ተንኰለኛ ናቸው።

አምላክን መስሎ ቴዎድሮስ

ንዑና ሑሩ ሲል ዋለ ጎሙስ።

(እራሳቸው የገጠሙዋቸው)።

ተገፍቶ ተገፍቶ ሸፍቶ ቢወጣ

አሁን ቅቤ ሆነ ላለም የሚበቃ።

ወንድሞቹ ሁሉ ወደ ኋላ ቀርተው

ደበደቡት አሉ ብቻውን አግኝተው።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

አንድ ወንድም ነበረ ሲጮኽ የሚረዳ

እኔ ብቻ አይደለሁ አገርም ተጐዳ።

ፍርሃትን ለጐንደር ፍርሃትን ለጐጃም ፍርሃትን

ለትግሬ ፍርሃትን ለወሎ ፍርሃትን ለሸዋ

እኔ አላስተምርም። ሽጉጤን ጠጥቼ እለዋለሁ

ኩርትም።

(በጭካኔያቸው ምክንያት የገጠሙት)።

አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ

እየለበለበ አቃጥሎ ይፍጃችሁ።

ሺሕ ፈረስ ከኋላው ሺህ ፈረስ ከፊቱ

ይህን ሳታይ ሞተች ኮሶ ሻጭ እናቱ።

ዐፄ ቴዎድሮስ እጅግ ተዋረዱ

የሸዋን ሕዝብ ሁሉ እጅ ነስተውት ሄዱ።

ሞጣ ቀራንዮ ምነው አይታረስ

በሬሳ ላይ መጣሁ ከዚያ እስከዚህ ድረስ።

አንጥረኛው ብዙ ከንጉሡ ቤት

ባላልቦ አደረጉት ይህን ሁሉ ሴት።

ስለ ጀብዷቸው የተገጠመ።

ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሣ ብሎ ስም

ዐርብ ዐርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም።

ሱሪህ አረንጓዴ ጐራዴህ ባለ ወርቅ

በጣም አምሮብሃል አንተ ብቻ ታጠቅ።

የታጠቅ ጐራዴ ብረት የነበረ

እየቀላ ሄደ ቱርክ እየመሰለ።

ታጠቅን ባል ብሎ ማን አምኖ ይቆርባል

ሴሰኛውን ጉበዝ ያራቱን ማዕዘን ባል።

አባትና እናቱ ያላንድ አልወለዱ

አባ ታጠቅ ካሣ ያው አንዱ ያው አንዱ። (ያ ወንዱ)።

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss

Telegram: Amharic Books t.me/amharicbookss